Amerigroup

District of Columbia











Amerigroup District of Columbia, Inc. Alliance

# የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ

DHCF
Department of Health Care Finance

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

1046354DCMAMAGP 06/23

## Amerigroup District of Columbia, Inc.

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን ሊደውሉልን፣ ወይም ቢሯችን ከሰኞ እስከ አርብ በምስራቃዊያን የሰዓት አቆጣጠር ከ 8:00 ኤኤም እስከ 6:00 ፒኤም መምጣት ይችላሉ። እንዴት እንደሚያገኙን አቅጣጫውን ለማወቅ፣ ይደውሉ በ 800-600-4441 (TTY 711)።


**ዋሽንግተን ዲሲ ቢሮ**
609 H Street NE, Ste. 200
Washington, DC 20002

የስራ ሰዓታት፡- ከ9:00 ኤኤም እስከ 5:00ፒኤም በምስራቃዊያን ሰዓት አቆጣጠር
800-600-4441 (TTY 711)

**English**

“If you do not speak and/or read English, please call 800-600-4441 (TTY 711) between Monday through Friday from 8:00 a.m. to 6:00 p.m. Eastern time. A representative will assist you.”

**Spanish**

“Si usted no habla ni lee inglés, llame al 800-600-4441 (TTY 711) de lunes a viernes de 8:00 a.m. a 6:00 p.m. hora del Este. Un representante le ayudará”

**Vietnamese**

“Nếu quý vị không nói và/hoặc đọc Tiếng Anh, vui lòng gọi 800-600-4441 (TTY 711) từ Thứ Hai đến Thứ Sáu từ 8:00 giờ sáng đến 6:00 giờ tối, giờ miền Đông. Một đại diện sẽ hỗ trợ quý vị.”

**Korean**

“영어를 구사하지 못하시거나 읽지 못하시는 경우 800-600-4441 (TTY 711)번으로 월요일-금요일 동부 시간으로 오전 8:00시에서 오후 6:00시까지 연락해 주십시오.담당자가 도와드릴 것입니다.”

**French**

“ Si vous ne parlez pas et/ou ne lisez pas l’anglais, veuillez appeler 800-600-4441 (TTY 711) du lundi au vendredi de 8:00 a.m. à 6:00 p.m., heure de l’Est. Un agent vous aidera. “

**Arabic**

"إذا كنت لا تتحدث و/أو تقرأ الإنكليزية، فيرجى الاتصال على الرقم (TTY 711) 800-600-4441 من الاثنين إلى الجمعة من الساعة 8:00 صباحًا وحتى الساعة 6:00 مساءً بالتوقيت الشرقي. وسوف يساعدك ممثل."

**Amharic**

“እንግሊዘኛ የማይናገሩ እና/ወይም የማያነቡ ከሆነ፣ እባክዎ ወደ 800-600-4441 (TTY 711) ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:00ኤኤም እስከ6:00ፒኤም በምስራቃዊያን ሰዓት አቆጣጠር ይደውሉ። ተወካይ ለእርስዎ እገዛ ያደርጋሉ።”

**Mandarin**

[如果您不会说和/或读英语，请致电 800-600-4441 (TTY 711)，服务时间：东部时间周一至周五 8:00 a.m.-6:00 p.m.。我们的服务代表将为您提供协助。]

**Russian**

«Если вы не говорите и/или не читаете по-английски, пожалуйста, позвоните по номеру 800-600-4441 (TTY: 711) с понедельника по пятницу с 8:00 до 18:00 по восточному времени. Наш представитель поможет вам»

**Burmese**

“အကယ်၍ သင် အင်္ဂလိပ်စကားပြောခြင်း သို့မဟုတ် စာဖတ်ခြင်းမရှိပါက၊ ကေ းဇူးပြု၍ တနင်္လာနေ့မှ သောကြာနေ့အကြား မနက် 8:00 နာရီမှ ညနေ 6:00 နာရီ ( အရှေ့စံတော်ချိန်) တွင် 800-600-4441 (TTY 711) သို့ခေါ်ဆိုနိုင်ပါသည်။ ကိုယ်စားလှယ်တစ်ဦးသည် သသင့်အား အကူအညီပေးပါမည်”

DHCF vs 06/1/2023

**Cantonese**
[如果您不會說和/或讀英語，請致電 800-600-4441 (TTY 711)，服務時間： 東部時間週一至週五8:00 a.m.-6:00 p.m.。我們的服務代表將為您提供協助。]

**Farsi**
«اگر نمی‌توانید به انگلیسی صحبت کنید و/یا بخوانید، لطفاً با شماره  (TTY 711) 800-600-4441 از دوشنبه تا جمعه از ساعت 8:00 صبح تا 6:00 بعدازظهر به زمان شرقی تماس بگیرید. یک نماینده به شما کمک خواهد کرد.»

**Polish**
Jeśli nie potrafisz mówić i/lub czytać po angielsku, zadzwoń pod numer 800-600-4441 (TTY 711) od poniedziałku do piątku w godzinach od 8:00 a.m. do 6:00 p.m. czasu wschodniego. Przedstawiciel udzieli Ci pomocy.

**Portuguese**
"Caso não seja capaz de falar e/ou ler em inglês, telefone para o número 800-600-4441 (TTY 711) de segunda a sexta-feira, das 8:00 a.m. às 6:00 p.m., ET. Teremos um assistente disponível para lhe prestar apoio."

**Punjabi**
"ਜੇ ਤੁਸੀਂ ਅੰਗਰੇਜ਼ੀ ਨਹੀਂ ਬੋਲਦੇ ਅਤੇ/ਜਾਂ ਪੜ੍ਹਦੇ ਨਹੀਂ ਹੋ, ਤਾਂ ਕਿਰਪਾ ਕਰਕੇ ਸੋਮਵਾਰ ਤੋਂ ਸ਼ੁੱਕਰਵਾਰ ਵਿਚਕਾਰ ਈਸਟਰਨ ਸਮੇਂ ਅਨੁਸਾਰ ਸਵੇਰੇ 8:00 ਵਜੇ ਤੋਂ ਸ਼ਾਮ 6:00 ਵਜੇ ਤੱਕ 800-600-4441 (TTY 711) 'ਤੇ ਕਾਲ ਕਰੋ। ਇੱਕ ਨੁਮਾਇੰਦਾ ਤੁਹਾਡੀ ਸਹਾਇਤਾ ਕਰੇਗਾ।"

**Haitian Creole**
"Si ou pa pale oubyen li anglè, tanpri rele 800-600-4441 (TTY 711) de lundi a vendredi de 8:00 a.m a 6:00 p.m lé de lest. Youn reprezantan ap ede'w."

**Hindi**
यदि आप अंग्रेज़ी नहीं बोलते हैं और/या पढ़ते नहीं हैं, तो कृपया 800-600-4441 (TTY 711) पर सोमवार से शुक्रवार के बीच ईस्टर्न समय के अनुसार सुबह 8:00 बजे से शाम 6:00 बजे तक कॉल करें। एक प्रतिनिधि आपकी मदद करेगा।

**Somali**
"Haddii aanad ku hadlin iyo/ama akhriyin Ingiriisiga, fadlan soo wac 800-600-4441 (TTY 711) inta u dhaxaysa Isniinta ilaa Jimcaha laga bilaabo 8:00 subaxnimo ilaa 6:00 fiidnimo Wakhtiga bariga. Wakiil ayaa ku caawin doona."

**Hmong**
"Yog tias koj tsis paub hais thiab/los sis nyeem ntawv Askiv, thov hu rau 800-600-4441 (TTY 711) nyob rau Hnub Monday txog Hnub Friday thaum 8:00 teev sawv ntxov txog 6:00 teev tsaus ntuj raws lub sij hawm Sab Hnub Tuaj. Yuav muaj ib tug neeg sawv cev los pab koj."

**Italian**
"Se non parlate e/o non leggete l'inglese, chiamate il numero 800-600-4441 (TTY 711) dal lunedì al venerdì dalle 8:00 a.m. alle 6:00 p.m. EST. Un rappresentante Vi assisterà."

**Tagalog**
"Kung hindi ka nagsasalita at/o nagbabasa ng Ingles, mangyaring tumawag sa 800-600-4441 (TTY 711) sa pagitan ng Lunes hanggang Biyernes mula 8:00 a.m. hanggang 6:00 p.m. oras sa Silangan.  Isang kinatawan ang tutulong sa iyo."

**Japanese**
[英語がわからない場合は、月曜から金曜の8 a.m.-6 p.m.（東部標準時）の間に 800-600-4441（TTY 711）までお電話ください。担当者がサポートいたします。]

## <u>ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ስለ የተቀናጀ የእንክብካቤ ድርጅት (MCO) ጥያቄዎች፥** | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ) | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| | TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 711 (ከክፍያ ነፃ) | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| **የሐኪምዎ ቢሮ ከተዘጋ በኋላ ህክምና ካስፈለገት፥** | የነርስ የስልክ መስመር | 800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ) | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| | TTY/TDD የነርስ የስልክ መስመር | 711 (ከክፍያ ነፃ) | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| **በ24 ሰዓታት ውስጥ ሐኪም ማየት የሚያስፈልግዎ ከሆነ (“አስቸኳይ ሕክምና”)፥** | የእርስዎ <u>PCP</u> ቢሮ | (የእርስዎን የ <u>PCP</u> መረጃ እዚህ ይሙሉ) | |
| | የነርስ የስልክ መስመር | 800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ) | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| **ወደ ቀጠሮ ለመሄድ ትራንስፖርት ካስፈለግዎ፥** | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | Medical Transportation Management, MTM<br>24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት<br>888-828-1081 (TTY 711) (ከክፍያ ነጻ) | |
| **የአእምሮ ጤና ሕክምና ካስፈለገት ወይም የአእምሮ ጤና ጥያቄ ካሎት፥** | የእርስዎ <u>PCP</u> ቢሮ | (የእርስዎን የ <u>PCP</u> መረጃ እዚህ ይሙሉ) | |
| | የነርስ የስልክ መስመር | 800-600-4441 (TTY 711) (ከክፍያ ነፃ) | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| | የDC የአእምሮ ጤና ዲፓርትመንት የስልክ መስመር | 1 (888) 793-4357 | 24ሰዓት በቀን፣ 7ቀናት በሳምንት |
| **ቋንቋዎን መናገር የሚችል ሰው ከፈለጉ ወይም መስማት የተሳነዎ ከሆኑ፥** | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 800-600-4441 (ከክፍያ ነጻ) | ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ8:00 ኤኤም እስከ6:00ፒኤም በምስራቃዊያን የሰዓት አቆጣጠር |
| | TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 711 (ከክፍያ ነፃ) | ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ8:00 ኤኤም እስከ6:00ፒኤም በምስራቃዊያን የሰዓት አቆጣጠር |
| **የጥርስ ህክምና ጥያቄዎች፥** | Avesis | 833-554-1012 | ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ7:00ኤኤም እስከ8:00ፒኤም በምስራቃዊያን የሰዓት አቆጣጠር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የዓይን ህክምና ጥያቄዎች፥** | Avesis | 833-554-1012 | ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ7:00 ኤኤም እስከ8:00ፒኤም በምስራቃዊያን የሰዓት አቆጣጠር |
| **ለድንገተኛ ሁኔታ፣ ወደ911ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ** | | | |

## የግል መረጃ

**የእኔ የአሊያንስ መታወቂያ ቁጥር፥**

---

**የኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP)፥**

---

**የኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) አድራሻ፥**

---

**የኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) ስልክ፥**

---

**የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) ስም፥**

---

**የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) አድራሻ፥**

---

**የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP)፥**

---

## ማውጫ


**ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች ........ 5**

**እንኳን ወደ Amerigroup DC በደህና መጡ ........ 10**

ስለዚህ MCO ........ 10

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል ........ 10

**መብቶችዎ ........ 11**

**ግዴታዎችዎ ........ 12**

**የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ቁጥር ........ 13**

**የእርስዎ ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP) ........ 14**

PCP ምንድን ነው? ........ 14

የእርስዎን PCP እንዴት እንደሚመርጡ? ........ 14

የእርስዎን PCP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ? ........ 15

**ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) ........ 15**

PDP ምንድን ነው? ........ 15

የእርስዎን PDP እንዴት እንደሚመርጡ? ........ 15

የእርስዎን PDP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ? ........ 16

**መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ እና ድንገተኛ ህክምና ........ 17**

መደበኛ ህክምና ........ 17

አስቸኳይ ህክምና ........ 17

ድንገተኛ ህክምና (ድንገተኛ ህክምና ቢያጋጥምዎ ምን ማድረግ እንደሚችሉ) ........ 17

**ከከተማ ውጭ ሲሆኑ ህክምና ........ 18**

**በመረብ ውስጥ እና ከመረብ ውጭ አቅራቢዎች ........ 18**

**ቀጠሮ ማስያዝ ........ 19**

የእርስዎ PCP ወይም PDP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ ........ 19

ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ ........ 20

የእርስዎ የPCP ወይም የPDP ቢሮ ዝግ በሚሆንበት ጊዜ ህክምና ማግኘት ........ 20

ቀጠሮ ለማግኘት የመጠበቂያ ጊዜ ........ 20

**የድጋፍ አገልግሎቶች ........ 21**

የትራንስፖርት አገልግሎቶች ........ 21

እንግሊዘኛ በሚገባ መናገር የማይችሉ ከሆነ ያሉት አገልግሎቶች ..... 21

የመስማት ወይም ማየት ችግር ካለብዎ ያለዎ አገልግሎቶች ..... 22

**የስፔሺያሊቲ ህክምና እና ሪፈራሎች ..... 22**

የስፔሺያሊቲ ህክምና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል (“ሪፈራል” ምንድን ነው?) ..... 22

የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች ..... 23

የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ..... 23

የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች እና የሐኪም ማዘዣ ያላቸው መድሃኒቶች ..... 24

የበሽታ መቆጣጠር ..... 25

የህክምና ቅንጅት እና የጉዳይ ፍሰት ፕሮግራሞች ..... 26

**ከመታመም የሚከላከልልዎ አገልግሎቶች ..... 26**

የምርመራዎች (“ማጣሪያዎች”) ምክረሀሳቦች ..... 26

እንዴት ጤናማ ሆኖ መቆየት እንደሚቻል ..... 27

ክትባቶች ወይም "መርፌዎች" ..... 27

**እርግዝና - መውለድ ..... 27**

ከወሊድ በፊት እና በኋላ ..... 28

**የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች ..... 29**

በAmerigroup DC የሚሸፈኑ አገልግሎቶች ..... 29

በAmerigroup DC የማይሸፈኑ አገልግሎቶች ..... 31

**ሌላ ጠቃሚ መረጃ ..... 32**

ቦታ ከቀየርኩስ? ..... 32

ልጅ ከወለድኩስ? ..... 32

ልጅ በማደጎ ከወሰድኩስ? ..... 32

ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞትስ? ..... 32

የኔን MCO እንዴት መቀየር እንደምችል? ..... 32

ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ቢደርሰኝስ? ..... 33

ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ይከፍላሉ? ..... 33

የቀደመ መመሪያ ..... 33

ሐኪሞችዎን እንዴት እንደምንከፍላቸው ልዩ መረጃ ..... 34

ማጭበርበር ..... 34

**ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ...... 34**

ቅሬታዎች ...... 34

ይግባኞች ...... 35

ፍትሃዊ ችሎቶች ...... 35

የተፋጠነ (ድንገተኛ) ቅሬታዎች እና የይግባኞች ሂደት ...... 36

በቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ሂደት ውስጥ እርስዎ ያሎት መብቶች ...... 37

**የግላዊነት ልምድ ማስታወቂያ ...... 37**

**የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ ...... 43**

**ትርጉሞች ...... 44**

## **እንኳን ወደ Amerigroup DC በደህና መጡ**

Amerigroup District of Columbia, Inc.ን እንደ የጤና እቅድዎ ስለመረጡ እናመሰግናለን። እኛ የDC Healthcare Alliance ፕሮግራም ተመዝጋቢዎችን በማገልገላችን ኩራት ይሰማናል።

ይህ የተመዝጋቢ መመሪያ መጽሐፍ ስለ Amerigroup DC እና የጤና እቅድዎ እንዴት እንደሚሰራ ጠቃሚ መረጃ አለው። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት። እንደ Amerigroup DC ተመዝጋቢ እንደ መከላከያ ምርመራዎች፣ ምርመራዎች፣ መድሃኒቶች፣ እና የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ የመሳሰሉ መደበኛ የጤና ጥቅማጥቅሞች እና ጤናማ ኑሮ እንዲኖሩ እና ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎ የሚያግዙ ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች አሉት።

በየወሩ፣ አዲስ የተመዝጋቢ ገለጻ (ኦሪየንቴሽን) እናዘጋጃለን። ይህ ስለ Amerigroup DC ጥቅማጥቅሞችዎ የበለጠ የሚማሩበት ሌላ መንገድ ነው። በገለጻው ወቅት፣ ለጥያቄዎችዎ መልስ ለማግኘት ከቡድናችን አባል ጋር በተጨማሪ መነጋገር ይችላሉ። ከእኛ ጋር አሁኑኑ መነጋገር ይፈልጋሉ? ይደውሉልን እንገኛለን። ወደ መለያዎ (አካውንትዎ)ይግቡ ወይም በመስመር ላይ (ኦንላይን) ይመዝገቡ ፣ በ myamerigroup.com/DC። ደህንነቱ የተጠበቀ የጽሁፍ መልእክት ይላኩልን ወይም የስልክ ቀጠሮ ያስይዙ። ወይም ወደኛ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711)፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:00ኤኤም እስከ6:00ፒኤም በምስራቃዊ የሰዓት አቆጣጠር ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ። እኛ እዚህ ያለነው እርስዎን በእያንዳንዱ እርምጃ ለማገዝ ነው።

### **ስለዚህ MCO**

በጤና ህክምና እና በሐኪም የሚገለጹ ቃላት አንዳንድ ጊዜ ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው። Amerigroup DC የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ ማግኘት እንዲችሉ ለማገዝ በColumbia ዲስትሪክት ክፍያ የሚከፈል ቁጥጥር የሚደረግበት የህክምና እቅድ ነው። በዚህ የመምሪያ መጽሃፍ፣ እኛ Amerigroup DC እንዴት እንደሚሰራ፣ ሐኪሞችን እንዴት እንደሚያገኙ፣ ወደኛ እንዴት መደወል እንደሚችሉ፣ እና እኛ ስለምንከፍላቸው ነገሮች እንነግርዎታለን። በትርጉሞች ክፍል፣ የእነዚህን ቃላት ፍቺ በዚህ መጽሃፍ ጀርባ ላይ አብራርተናል።

በዚህ መጽሃፍ ስላነበቡት ነገሮች ጥያቄዎች ካሉት፣ ወይም ስለ Amerigroup DC ሌሎች ጥያቄዎች ካሉት፣ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋርበ800-600-4441 (TTY 711) መደወል ወይም myamerigroup.com/DC መጎብኘት ይችላሉ፣ እና እኛ እርስዎን ለማገዝ የተቻለንን እናደርጋለን።

### **ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል**

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ የሚከተሉትን ይነግርዎታል፥

- የጤና እንክብካቤን እንዴት እንደሚያገኙ
- ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶችዎን
- ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች
- ዋና የህክምና አቅራቢዎን እና ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢዎን (የእርስዎ PCP ወይም PDP) እንዴት መምረጥ እንደሚቻል

- ሲታመሙ ምን ማድረግ እንዳለብዎ
- ቅሬታ ካሉት ወይም Amerigroup DC የሰጠውን ውሳኔ ማስለወጥ (ይግባኝ ማለት) ከፈለጉ ምን ማድረግ እንዳለብዎ

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ Amerigroup DC እንደሚሰራ መሰረታዊ መረጃ ይሰጥዎታል። ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉት እባክዎ ወደ Amerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በማንኛውም ጊዜ፣ 24ሰዓት በቀን እና7ቀናት በሳምንት ይደውሉ።

## <u>መብቶችዎ</u>

- ከሐኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች ጋር ሲያወሩ፣ ሚስጥራዊ መሆኑን ማወቅ
- በሚረዱት ቋንቋ በሽታው ወይም ሕክምናው እንዲገለጽልዎ መደረግ
- ስለ ሕክምናዎ በሚደረጉ ውሳኔዎች መሳተፍ፣ ሕክምና ያለመቀበል መብትን ጨምሮ
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ የተሟላ፣ ግልጽ እና ለመረዳት የሚቻል የሕክምና አማራጮችን እና የእያንዳንዱን አማራጭ አደጋ ማብራሪያ ማግኘት
- እንክብካቤ ወይም ሕክምና ማግኘት አለመፍቀድ
- ለማስገደድ፣ ለዲስፒሊን፣ ለምቾት፣ ወይም ለበቀል ዓላማ ከሚደረጉ ማንኛውም ገደቦች ወይም የመገለል ሁኔታዎች ነጻ መሆን
- የሕክምና ሪከርዶችዎን ማየት እና ቅጂ ማግኘት እንዲሁም ስህተት ካለበት እንዲሻሻል ወይም እንዲቀየር የመጠየቅ
- ያሉትን እና ለእርስዎ ተደራሽ የሆኑትን የጤና ሕክምና አገልግሎቶችን በተገቢው ጊዜ ማግኘት
- ብቁ የሆነ PCP/PDP ከ Amerigroup DC መረብ ውስጥ መምረጥ እና የእርስዎን PCP/PDP መቀየር
- ስላገኙት ሕክምና ቅሬታ ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት
- Amerigroup DC አገልግሎት ወይም እቃ በመከልከል፣ በመቀነስ ወይም በማቋረጥ ትክክል አይደለም ብለው ካመኑ፣ ይግባኝ ወይም ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ
- ከሚመርጡት አቅራቢ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶችን ማግኘት
- ያለ አላስፈላጊ መዘግየት የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት
- በመረቡ ውስጥ ካለ፣ ወይም አስፈላጊ ከሆነ፣ ከመረብ ውጭ ካለ ብቃት ያለው የጤና ሕክምና ባለሞያ እርስዎ አንዳች ወጪ ሳያወጡ ሁለተኛ አስተያየት ማግኘት
- የቀደመ መመሪያዎች ላይ መረጃ ማግኘት እና ማንኛውም የህይወት ማቆያ ሕክምናን ያለማግኘት ወይም ማግኘት መቀጠልን መምረጥ
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ እና የአቅራቢ ማውጫ ቅጂን ማግኘት
- አዲስ የሕክምና እቅድ እስኪያገኙ ድረስ አሁን እያገኙ ያለውን ሕክምና ማግኘት መቀጠል
- ከክፍያ ነጻ የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶችን ማግኘት

- የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን ማግኘትን አለመቀበል
- ከክፍያ ነጻ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ማግኘት
- የቀደመ ፈቃድ ሂደቶች ላይ ማብራሪያ ማግኘት
- ስለ የAmerigrioup DC የገንዘብ ሁኔታ እና ለሐኪሞቻችን ክፍያ ስለምንፈጽምበት ማንኛውም ልዩ ዘዴዎች መረጃ ማግኘት
- የደምበኛ እርካታ የዳሰሳ ጥናቶች ማጠቃለያዎችን ማግኘት
- የመድሃኒት ማዘዣ ላላቸው መድሃኒቶች የAmerigroup DC "በተጻፈው መሰረት ይጠቀሙ" የሚል ፖሊሲ ማግኘት
- ሽፋን ያላቸውን የሁሉንም መድሃኒቶች ዝርዝር ማግኘት
- ሰብዓዊነትዎን እና የግል ነጻነት መብቶን ባከበረ መልኩ በክብር መታከም

## ግዴታዎችዎ

- ህክምና የሚሰጥዎትን ሰዎች በአክብሮት እና በክብር መያዝ
- የDC Medicaid የተቀናጀ የሕክምና ፕሮግራም እና የAmerigroup DC ህጎችን ማክበር
- ሐኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች የሚሰጥዎትን መመሪያዎች መተግበር
- በተያዙት ቀጠሮዎች መገኘት
- ቀጠሮውን መሰረዝ ካለብዎ ቢያንስ ከ24 ሰዓታት በፊት ለሐኪምዎ መንገር
- የሐኪምዎ ትእዛዝ ካልገባዎ ተጨማሪ ማብራሪያ መጠየቅ
- ድንገተኛ ሕክምና ሲያፈልግዎ ብቻ ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ
- ጤናዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለ ሚችሉ የሕክምና እና የግል ችግሮች ለእርስዎ PCP/PDP መንገር
- እርስዎ ወይም የቤተሰብ ተመዝጋቢ ሌላ የጤና መድን ካላችሁ ወይም የአድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ለውጥ ካለ ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና Amerigroup DC ሪፖርት ማድረግ።
- በቤተሰብዎ ውስጥ ማንኛውም ለውጥ ካለ (ማለትም፥ ሞት፣ ወሊድ፣ ወዘተ) ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና Amerigroup DC ሪፖርት ማድረግ
- የጤና ችግሮችዎን ለመረዳት መሞከር እና የሕክምና ግቦች ዝግጅት ላይ መሳተፍ
- ሐኪምዎ ከዚህ በፊት እርስዎን ካከሙ አቅራቢዎች የሕክምና ሪከርዶችዎን እንዲያገኙ ማገዝ
- በአደጋ ምክንያት ወይም ሥራ ላይ ከተጎዱ ለAmerigroup DC ማሳወቅ

## <u>የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ቁጥር</u>

ዋና የሕክምና አቅራቢ (PCP) አንድ ጊዜ ከተመደበልዎ በኋላ፣ የተመዝጋቢ የመታወቂያ ካርድ በፖስታ እንልክልዎታለን። ይህ ካርድ የእርስዎ ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች፣ የመድሃኒት መደብሮች፣ እና ሌሎች እርስዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ መሆንዎን እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። እባክዎ በተመዝጋቢ የመታወቂያ ካርድዎ ላይ ያለው መረጃ ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ። ማንኛውም ችግሮች ካሉ፣ ወይም ካርድዎ ከጠፋብዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)- እያንዳንዱ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ የራሳቸው ካርድ አላቸው። በተጨማሪ የእርስዎም ልጆች የራሳቸው ካርድ ይኖራቸዋል። እንዳይጠፉ የልጆችዎን ካርድ እርስዎ መያዝ አለብዎ። የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ማንኛውም ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ በህግ የተከለከለ ነው።

### የተመዝጋቢ የመታወቂያ ካርድዎ ይህን ይመስላል፥

### የካርዱ ፊትለፊት

Amerigroup
District of Columbia

Effective Date:
Date of Birth:
Amerigroup DC #: **123456789**

**myamerigroup.com/DC**
Enrollee Name: **JOHN Q SAMPLE**
DC Healthcare Alliance Program Number:
Primary Care Provider (PCP):
PCP Telephone #:
Primary Dental Provider (PDP):
PDP Telephone #:
Vision: **833-554-1012** Dental: **833-554-1012**
Pharmacy: RxBIN: 020107; RxPCN: FC; RxGRP: RX8489

### የካርዱ ጀርባ

**Keep this card with you at all times | Call 911 if you think you have a medical emergency**
Enrollee Services/24-hour Nurse HelpLine: **800-600-4441 (TTY 711)**
Behavioral Health Crisis Line: **844-405-4300 (TTY 711)**
Pharmacy Enrollee Services: **833-214-3604**
Transportation Services: **888-828-1081 (TTY 711)**
Economic Security Administration (ESA): **202-727-5355**
**PROVIDERS:** Certain services must be preauthorized. Care that is not preauthorized may not be covered. For preauthorization/billing information, call **800-454-3730.** For preauthorization of medications, call **800-454-3730. SUBMIT MEDICAL CLAIMS TO:** AMERIGROUP DC P.O. BOX 61010 VIRGINIA BEACH, VA 23466-1010

DHCF Department of Health Care Finance

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

Amerigroup complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex.

DC01 04/23

እባክዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እና ፎቶግራፍ ያለበት መታወቂያ ሁልጊዜ መያዝ ያስታውሱ። ማንኛውም የህክምና እንክብካቤ ከማግኘትዎ በፊት ወይም ከመድሃኒት ቤት መድሃኒት ከመውሰድዎ በፊት ሁልጊዜ ካርድዎን ያሳዩ።

## <u>የእርስዎ ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)</u>

### PCP ምንድን ነው?

እርስዎ አሁን የAmerigroup DC ተመዝጋቢ በመሆንዎ፣ የእርስዎ PCP እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ይረዳዎታል።

ሕክምና ሲያስፈልግዎ መጀመሪያ የእርስዎ PCP ጋር መደወል አስፈላጊ ነው። ወደ Amerigroup DC ከመመደብዎ በፊት PCP ከነበሮት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711)ይደውሉ። ከፈለጉ ከዚያ PCP ጋር እንዲቆዩ ልንረዳዎ እንችላለን።

### የእርስዎን PCP እንዴት እንደሚመርጡ?

1. እርስዎ Amerigroup DC ጋር ሲመዘገቡ PCP ይምረጡ። ይህ ሰው የAmerigroup DC ተመዝጋቢ ሆነው በሚቆዩበት ጊዜ የእርስዎ PCP ይሆናሉ።
   - የእርስዎ የአሁን PCP የAmerigroup DC መረብ አቅራቢ ከሆኑ፣ ከዚያ ሐኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
   - እርስዎ PCP ከሌሎት፣ ከኛ የአቅራቢ ማውጫ ካለው ዝርዝር ወይም myamerigroup.com/DC ጋር መምረጥ ይችላሉ።
   - ሐኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋርበ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
   - በAmerigroup DC ውስጥ በተካተቱ በመጀመሪያዎቹ10ቀናት ውስጥ PCP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ ሐኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PCP ካልወደዷቸው፣ የእርስዎን PCP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎን PCP ለመቀየር የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
   - Amerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። ካርድዎ የእርስዎን የPCP ስም እና የስልክ ቁጥር ይኖረዋል።

2. በAmerigroup DC ውስጥ ላሉት ለእያንዳንዱ የቤተሰብ ተመዝጋቢ PCP ይምረጡ። የእርስዎ PCP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፥
   - የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቡን ሁሉ ሊያክሙ ይችላሉ።
   - የውስጥ ደዌ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ አዋቂ እና እድሜያቸው14እና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆችን ብቻ ያክማሉ።
   - አዋላጅ ሐኪም/የማህጸን ሐኪም (OB/GYN) - የሴቶች ጤና እና የወሊድ ሕክምና ላይ ያተኮረ

- እርስዎ ልዩ የጤና ሕክምና የሚያስፈልጎት ከሆነ፣ ስፔሺያሊስትን እንደ PCP መምረጥ ይችላሉ።

3. የእርስዎን PCP ሲመርጡ፣ እባክዎ የሚከተሉትን ያድርጉ፦
   - ለቤትዎ ወይም ለሥራዎ አቅራቢያ የሆነ ሐኪም ይምረጡ።
   - ሁሉም ሐኪሞች ታካሚዎችን ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። ወደሚፈልጉት ሆስፒታል ሊልክዎ የሚችሉ ሐኪም ይምረጡ።
   - አንዳንድ ጊዜ፣ የሚመርጡት PCP አዲስ ታካሚዎችን መቀበል አይችልም። የኛ የአቅራቢ ማውጫ አንድ PCP እርስዎን ወደየትኞቹ ሆስፒታል ሊልክዎ እንደሚችል ይዘረዝራል። በተጨማሪ ለእርዳታ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
   - ሌላ ሐኪም መመረጥ የሚኖርብዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

## የእርስዎን PCP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ?

የእርስዎን PCP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። አዲስ PCP ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ። ከአቅራቢ ማውጫ አዲስ PCP መመረጥ ብቻ ነው። አዲስ PCP ከመረጡ በኋላ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋርበ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## <u>ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP)</u>

## PDP ምንድን ነው?

እርስዎ አሁን የAmerigroup DC ተመዝጋቢ በመሆንዎ፣ የእርስዎ PDP እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ይረዳዎታል።

ሕክምና ሲያስፈልግዎ መጀመሪያ የእርስዎ PDP ጋር መደወል አስፈላጊ ነው። ወደ Amerigroup DC ከመመደብዎ በፊት የጥርስ ሀኪም ከነበሮት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ከፈለጉ ከዚያ PDP ጋር እንዲቆዩ ልንረዳዎ እንችላለን።

## የእርስዎን PDP እንዴት እንደሚመርጡ?

1. እርስዎ Amerigroup DC ጋር ሲመዘገቡ PDP ይምረጡ። ይህ ሰው የAmerigroup DC ተመዝጋቢ ሆነው በሚቆዩበት ጊዜ የእርስዎ PDP ይሆናሉ።
   - የእርስዎ የአሁን PDP የAmerigroup DC መረብ አቅራቢ ከሆኑ፣ ከዚያ ሐኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
   - እርስዎ PDP ከሌሎት፣ ከኛ የአቅራቢ ማውጫ ካለው የጥርስ ሐኪሞች ዝርዝር ወይም myamerigroup.com/DC ጋር መምረጥ ይችላሉ።
   - የጥርስ ሐኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

- በእኛ እቅድ ውስጥ በተካተቱ በመጀመሪያዎቹ10ቀናት ውስጥ PDP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ የጥርስ ሐኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PDP ካልወደዷቸው፣ የእርስዎን PDP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎን PDP ለመቀየር የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
- Amerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። ካርድዎ ላይ የእርስዎን የPDP ስም እና የስልክ ቁጥር ይኖረዋል።

2. በእኛ እቅድ ውስጥ ያሉ የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ ቤተሰብ PDP ይምረጡ። የእርስዎ PDP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፥
   - የቤተሰብ እና አጠቃላይ የጥርስ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቡን ሁሉ ሊያክሙ ይችላሉ።
3. የእርስዎን PDP ሲመርጡ፣ እባክዎ የሚከተለውን ያስተውሉ፡-
   - የኛ የአቅራቢ ማውጫ አንድ PDP እርስዎን ወደየትኞቹ ሆስፒታል ሊልክዎ እንደሚችል ይዘረዝራል። በተጨማሪ ለእርዳታ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
   - አንዳንድ ጊዜ፣ የሚመርጡት PDP አዲስ ታካሚዎችን መቀበል አይችልም። ሌላ የጥርስ ሐኪም መመረጥ የሚኖርብዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

## የእርስዎን PDP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ?

የእርስዎን PDP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአቅራቢ ማውጫ አዲስ PDP መመረጥ ብቻ ነው። አዲስ PDP ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ። አዲስ PDP ከመረጡ በኋላ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## <u>መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ እና ድንገተኛ ህክምና</u>

ሶስት (3) አይነት የጤና እንክብካቤ ሊያስፈልግዎ ይችላል፥ መደበኛ፣ አስቸኳይ ወይም ድንገተኛ።

### መደበኛ ህክምና

መደበኛ ሕክምና ማለት ከእርስዎ PCP የሚያገኙት መደበኛ ሕክምና ማለት ነው። መደበኛ ሕክምና የእርስዎ PCP ከላክዎት ሌሎች ሐኪሞች የሚያገኙት ሕክምናንም ይጨምራል። መደበኛ ሕክምና የክትትል ምርመራ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ምርመራ፣ እና የስኳር፣ የደምግፊት፣ እና አስም የመሳሰሉ የጤና ችግሮች ሕክምና ሊሆን። መደበኛ ሕክምና ካስፈለጎት፣ የእርስዎ የPCP ቢሮ ጋር ይደውሉ እና ቀጠሮ ለመያዝ ይጠይቁ።

### አስቸኳይ ህክምና

አስቸኳይ ሕክምና ማለት ወዲያውኑ ሳይሆን በ24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ የሕክምና እንክብካቤ ማለት ነው። አንዳንድ አስቸኳይ የሕክምና ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፥

- ማስታወክ
- ራስ ምታት
- ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን ከመጠን በላይ መጠቀም
- አነስተኛ ቃጠሎ ወይም ጥቃቅን ቁስል
- የጉሮሮ ህመም
- የአእምሮ ጤና
- የጆሮ ህመም
- የጡንቻ መሸማቀቅ/መወጠር
- ከ101 ዲግሪ ፋራናይት በላይ ትኩሳት

**አስቸኳይ ሕክምና የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ የእርስዎ የ PCP ቢሮ ጋር ይደውሉ።** የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ጊዜ የስልክ ጥሪ የሚቀበለው ሰው ጋር መልእክት ያስቀምጡ። ከዚያ የነርስ የእርዳታ የስልክ መስመር ጋር በ800-600-4441 (TTY 711)ይደውሉ። ነርሱ/ሷ ሐኪም ጋር ወዲያውኑ መሄድ ያለብዎ መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ያግዝዎታል። ነርሱ/ሷ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ ይነግርዎታል። ለመደበኛ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም አያስፈልግዎትም።

### ድንገተኛ ህክምና (ድንገተኛ ህክምና ቢያጋጥምዎ ምን ማድረግ እንደሚችሉ)

ድንገተኛ ሕክምና ማለት ለከባድ እና ድንገተኛ (አንዳንድ ጊዜ ለህይወት አስጊ የሆነ) ጉዳት ወይም በሽታ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎ የሕክምና እንክብካቤ ማለት ነው። ለድንገተኛ ሕክምና ማንኛውንም ሆስፒታል የመጠቀም መብት አሎት። ለድንገተኛ የሕክምና አገልግሎቶች የቀደመ ፈቃድ አያስፈልግም።

- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ሕመም
- ራስን መሳት
- የማይቆም በጣም ከባድ የደም መፍሰስ
- በጣም ከባድ ቃጠሎ
- ኮንቨልዥን ወይም ሲዠር ተብሎ የሚጠራ መንቀጥቀጥ
- እየተባባሰ የሚሄድህ ህመም

**ድንገተኛ ህክምና ሲያጋጥምዎ ምን ማድረግ እንደሚችሉ**

1. **ይደውሉ ወደ9-1-1ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል (ER) ይሂዱ።**
2. **ለ ER የእርስዎን የAmerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ያሳዩ።**
3. **በተቻልዎ ፍጥነት፣ የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ።**

## <u>ከከተማ ውጭ ሲሆኑ ህክምና</u>

ከከተማ ውጭ ሆነው በሐኪም መታየት ወይም መድሃኒት መውሰድ ካስፈለጎት፣

### መደበኛ ህክምና

ከከተማ ውጪ ሐኪም ጋር ወይም ሌላ አቅራቢ ጋር ሲሄዱ ለሐኪም የምንከፍልልዎ መሆን አለመሆኑን ወደኛ ደውለው መጠየቅ አለብዎ ምክንያቱም በColumbia ዲስትሪክት ውስጥ ያልሆኑ ሐኪሞች የAmerigroup DC አካል አይደሉም። ሕክምናውን ከማግኘትዎ በፊት Amerigroup DC እንደሚቻል ካልነገሮት፣ የሚከፍሉት እርስዎ እራስዎ ኖት። ከከተማ ውጭ ሆነው ከሐኪም መድሃኒት ካስፈለግዎ፣ የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ። እርዳታ ከፈለጉ የነርስ የእርዳታ መስመር ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

### አስቸኳይ ህክምና

ወደ PCPዎ መደወል አለብዎ። የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ የነርስ የእርዳታ ስልክ መስመር ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ነርሱ/ሷ ሐኪም ጋር ወዲያውኑ መሄድ ያለብዎ መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ያግዝዎታል። ነርሱ/ሷ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ ሊነግርዎ ይችላሉ። ለመደበኛ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም አያስፈልግዎትም።

### ድንገተኛ ሕክምና

የአእምሮ ጤና፣ የአልኮል፣ ወይም ሌላ የአደንዛዥ እጽ ድንገተኛ አደጋን ጨምሮ ድንገተኛ አደጋ ካለብዎ፣ አቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ህክምና ክፍል ER በአፋጣኝ ይሂዱ። ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል ከገቡ፣ የER ሰራተኞች ወደ እርስዎ PCP እንዲደውሉ መጠየቅ አለብዎ። ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል ከገቡ፣ በተቻለ ፍጥነት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይኖርብዎታል። **<u>ለድንገተኛ የሕክምና አገልግሎቶች የቀደመ ፈቃድ አያስፈልግም።</u>**

## <u>በመረብ ውስጥ እና ከመረብ ውጭ አቅራቢዎች</u>

Amerigroup DC ወደ አንዱ የኛ ሐኪም ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር ሲሄዱ ለእርስዎ ሕክምና ይከፍላል። እኛ እነዚህን ሐኪሞች እና ሌሎች የጤና ሕክምና አቅራቢዎች የኛ "መረብ" አቅራቢዎች ብለን እንጠራቸዋለን። የኛ ያልሆነ ሐኪም ወይም አቅራቢ "ከመረብ ውጪ" አቅራቢ ተብሎ ይጠራል። እነዚህ ሁሉም "የመረብ ውስጥ" ሐኪሞች በአቅራቢ ማውጫዎ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።

“ከመረብ ውጪ” የሆነ ሐኪም፣ ሆስፒታል፣ ወይም ላብራቶሪ ጋር ከሄዱ፣ ለሕክምናዎ መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል። መጀመሪያ እኛን ቢጠይቁን እና እኛ እንደሚቻል፣ አብዛኛውን ጊዜ በጽሁፍ፣ ነግሮኖት ቢሆን ኖሮ፣ መክፈል አይኖርብዎትም ነበር። እኛ ይህን "የቀደመ ፈቃድ" ብለን እንጠራዋለን።

**የቀደመ ፈቃድ (PA)** ማለት በመደበኛነት በAmerigroup DC ሽፋን ላልተሰጠው የጤና አገልግሎት ፈቃድ ማለት ነው። አገልግሎቱን ከማግኘትዎ በፊት ይህን ፈቃድ ማግኘት አለብዎ። ድንገተኛ ሕክምና ለማግኘት PA አያስፈልግዎትም። PA ስለ ማግኘት ለመጠየቅ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ከመረብ ውጪ ቢሆኑም፣ የመረጡት የቤተሰብ ምጣኔ አቅራቢ ጋር መሄድ ይችላሉ። የቀደመ ፈቃድ አያስፈልግም። ይመልከቱ ገጽ23.የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት።

በመረብ ውስጥ ያለ አቅራቢ ሽፋን ያለውን አገልግሎት ሊሰጥ ካልቻለ Amerigroup DC ከመረብ ውጪ ከሆነ አቅራቢ ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶችን በበቂ እና በትክክለኛ ጊዜ ይሰጣል።

## <u>ቀጠሮ ማስያዝ</u>

### የእርስዎ PCP ወይም PDP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ

- የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እና እርሳስ እና ወረቀት አጠገብዎ ያድርጉ።
- የእርስዎ PCP ቢሮ ጋር ይደውሉ። በተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎ ፊት ገጽ ላይ የእርስዎን PCP የስልክ ቁጥር ይፈልጉ። በተጨማሪም በእርስዎ የአቅራቢ ማውጫ ወይም ኦንላይን በmyamerigroup.com/DC ሊያገኙት ይችላሉ።
- ስልኩን ለሚያነሱት ግለሰብ እርስዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ እንደሆኑ ይንገሯቸው። የእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ መያዝ እንደፈለጉ ይንገሯቸው።
- ቀጠሮ መያዝ ለምን እንዳስፈለግዎት ለግለሰቡ ይንገሯቸው። ለምሳሌ፥
    a. ህመም እየተሰማዎ ነው።
    b. እራስዎን ጎድተዋል ወይም አደጋ አጋጥምዎታል።
    c. ምርመራ ወይም የክትትል ምርመራ ያስፈልግዎታል።
- የቀጠሮዎን ጊዜ እና ቀን ይጻፉት።
- በቀጠሮዎ ቀን በሰዓቱ ይገኙ እና የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እና ፎቶግራፍ ያለው መታወቂያ ይያዙ።
- ቀጠሮ ለማስያዝ እርዳታ ካስፈለጎት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።

### ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ

- በቀጠሮዎ መገኘት እና በሰዓቱ መምጣት በጣም አስፈላጊ ነው።
- ቀጠሮዎን መቀየር ወይም መሰረዝ ካለብዎ፣ እባክዎ ከቀጠሮዎ24ሰዓታት በፊት ወደ ሐኪምዎ ይደውሉ።
- ለአንዳንድ ቀጠሮዎች፣ ለመሰረዝ ከ24ሰዓታት የበለጠ ቀደም ብለው መደወል ሊኖርብዎ ይችላል።
- በቀጠሮዎ ላይ ካልተገኙ ወይም ከዘገዩ፣ ሐኪምዎ ታካሚያቸው እንደማይሆኑ ሊወስኑ ይችላሉ።

### የእርስዎ የPCP ወይም የPDP ቢሮ ዝግ በሚሆንበት ጊዜ ህክምና ማግኘት

ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ጊዜ የእርስዎን PCP ወይም PDP ማናገር ካስፈለግዎ፣ የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ጋር ይደውሉ እና ስልኩን የሚያነሱት ግለሰብ ጋር መልእክትዎን እና ስልክ ቁጥርዎን ያስቀምጡ። በተቻለ ፍጥነት አንድ ሰው ይደውልልዎታል። ይደውሉ ወደ911ወይም የድንገተኛ ሕክምና ክፍል ይሂዱ፣ ድንገተኛ ሁኔታ ካለብዎ። በተጨማሪ የነርስ የእርዳታ ስልክ መስመር ጋር24ሰዓታት በቀን በ800-600-4441 (TTY 711) መደወል ይችላሉ።

### ቀጠሮ ለማግኘት የመጠበቂያ ጊዜ

በደወሉ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ የሐኪምዎ ቢሮ ለእርስዎ ቀጠሮ ይሰጥዎታል። በእነዚህ ጊዜያት ቀጠሮ ማግኘት ካልቻሉ እባክዎ ወደ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ከታች ያለው ሰንጠረዥ ቀጠሮ ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ እንደሚፈጅ ያሳያል።

| **የጉብኝት ዓይነት** | **የእርስዎ ሁኔታ** | **ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል?** |
|---|---|---|
| **አስቸኳይ ጉብኝት** | ተጎድተዋል ወይም ታመዋል እና እንዳይብስብዎ በ24 ሰዓታት ውስጥ ሕክምና ያስፈልግዎታል፣ ነገር ግን አሁኑኑ ሐኪም ማየት አያስፈልግዎትም። አንዳንድ ምሳሌዎች አነስተኛ ቃጠሎዎች፣ የራስ ምታት፣ የጉሮሮ ህመም፣ ወይም የጡንቻ መሸማቀቅ/መወጠር ናቸው። | በ24ሰዓታት ውስጥ |
| **መደበኛ ጉብኝት** | አነስተኛ ህመም ወይም ጉዳት አለብዎ ወይም መደበኛ ምርመራ ያስፈልግዎታል፣ ነገር ግን አስቸኳይ ቀጠሮ አያስፈልግዎትም። | በ30ቀናት ውስጥ |
| **የክትትል ጉብኝት** | ከህክምናው በኋላ ዶክተርዎን ማየት ያስፈልግዎታል። በደንብ እየተሻሎት መሆኑን ብቻ ማረጋገጥ አለብት። | ከ1-2ሳምንታት ውስጥ፣ እንደ ሕክምናው ዓይነት |
| **የአዋቂ የደህንነት ምርመራ ጉብኝት** | • አዲስ ሐኪም ጋር የመጀመሪያ ቀጠሮዎን እየያዙ ነው<br>• መደበኛ የአዋቂ ምርመራዎ ደርሷል<br>• የፕሮስቴት ምርመራ፣ የፔልቪክ ምርመራ፣ የ PAP ስሚር፣ ወይም የጡት ምርመራዎ ደርሷል። | በ30ቀናት ውስጥ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከዚያ በፊት |

| ፔሺያሊስቶች ጋር አስቸኳይ ያልሆኑ ቀጠሮዎች (በሪፈራል) | የእርስዎ PCP አስቸኳይ ላልሆነ ሁኔታዎ ስፔሺያሊስት እንዲያዩ ሪፈር አድርጎዎታል። | በ30ቀናት ውስጥ |
|---|---|---|

## <u>የድጋፍ አገልግሎቶች</u>

### የትራንስፖርት አገልግሎቶች

ድንገተኛ ላልሆኑ ሁኔታዎች ወደ ሐኪም ቀጠሮ እና ወደ መድሃኒት ቤት ለመሄድ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

- የሕክምና የትራንስፖርት አስተዳደር (MTM) ጋር በ888-828-1081 ይደውሉ እና ስንት ሰዓት ላይ እና የትኛው ቀን ላይ እንዲያደርስዎ እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው።
- ትራንስፖርት ለማግኘት ከቀጠሮዎ ቢያንስ ከሁለት የሥራ ቀን በፊት (ቅዳሜን እና እሁድን አይጨምርም) መደወል አለብዎ።
- ወደ የቀደመ እና በየጊዜው የሚደረግ ማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና ሕክምና (EPSDT) ጉብኝቶች እና አስቸኳይ ለሆኑ ጉብኝቶች ትራንስፖርት የሚያስፈልግዎ ከሆነ፤ ትራንስፖርት ለመጠየቅ ከቀጠሮው ቀን በፊት መደወል ይችላሉ።
- የትራንስፖርቱ ዓይነቶች Uber (ኡበር)፣ Lyft (ሊፍት)፣ ባሶች፣ ሜትሮ፣ ለታክሲ የሚከፍሉት ደረሰኞች፣ የዊልቼይር ቫኖች፣ እና አምቡላንሶች ናቸው። የሚያገኙት የትራንስፖርት ዓይነት የሚወሰነው በሚያስፈልግዎ የሕክምና ዓይነት ነው።
- ለMTM የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን፣ የስልክ ቁጥርዎን፣ እና የሚነሱበትን ቦታ አድራሻ ይስጧቸው። በተጨማሪ፣ የሚሄዱበትን የሕክምና/የጥርስ ሕክምና ተቋም ወይም የሐኪም ቢሮ ስም፣ አድራሻ፣ እና ስልክ ቁጥር ይንገሯቸው።

Amerigroup DC በ Amerigroup DC ላልተሸፈኑ ነገር ግን በየጤና እንክብካቤ ፋይናንስ መምሪያ (DHCF) ወይም በሌላ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች ለተሸፈኑ የሐኪም ቀጠሮዎች የደርሶ መልስ ትራንስፖርት ይሰጣል። በተጨማሪ Amerigroup DC ለአብዛኛዎቹ ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ወደ/ከ ትራንስፖርት ያቀርባል።

### እንግሊዘኛ በሚገባ መናገር የማይችሉ ከሆነ ያሉት አገልግሎቶች

### የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

Amerigroup DC በሆስፒታሉ ውስጥ ጨምሮ የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን በነጻ ይሰጣል።

እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ ለአስተርጓሚ አገልግሎቶች። የአስተርጓሚ አገልግሎቶች የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ከሐኪም ቀጠሮዎ በፊት ያግኙን።

የአስተርጓሚ አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት በስልክ ነው። የሐኪም ቀጠሮዎ ላይ አስተርጓሚ ከእርስዎ ጋር እንዲገኙ ካስፈለገት፣ በ3-5 ቀናት ውስጥ ወይም በ48 ሰዓታት ውስጥ ለኛ ማሳወቅ አለብዎ። በአካል ፊት ለፊት የትርጉም አገልግሎትን የሚያስፈልግ ልዩ ሁኔታ ካለ፣ ተመዝጋቢዎቹ ወይም አቅራቢዎቹ ከAmerigroup DC የቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። ተመዝጋቢዎች ወይም አቅራቢዎች የፈቃድ ጥያቄን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለማስገባት የኛን የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ቡድንን ማነጋገር ይችላሉ።

### የትርጉም አገልግሎቶች

ከAmerigroup DC መረጃ ካገኙ እና ወደ ሌላ ቋንቋ እንዲተረጎምልዎ ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

### የመስማት ወይም ማየት ችግር ካለብዎ ያለዎ አገልግሎቶች

### መስማት እና ማየት ለተሳናቸው ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች

የመስማት ችግር ካለብዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ TTY 711። ይደውሉ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) የማየት ችግር ካጋጠመምዎ። እኛ ለእርስዎ መረጃ በኦዲዮ ቴፕ፣ በብሬል፣ ወይም በትልቅ እትመት ልንሰጦት እንችላለን።

## <u>የስፔሺያሊቲ ህክምና እና ሪፈራሎች</u>

### የስፔሺያሊቲ ህክምና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል (“ሪፈራል” ምንድን ነው?)

የእርስዎ ዋና የእንክብካቤ አቅራቢ (PCP) አብዛኛውን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን ሊያሟላ ይችላል፣ ነገር ግን ከሌላ የአቅራቢዎች አይነት እንክብካቤ ሊፈልጉ ይችላሉ። እኛ ለህክምና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች እንክብካቤዎችን ከሚሰጡ ከተለያዩ አይነት አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎት እንሰጣለን። እነዚህ አቅራቢዎች በልዩ የሕክምና መስክ ልዩ ስልጠና ስለወሰዱ ስፔሻሊስቶች ተብለው ይጠራሉ።

የስፔሻሊስቶች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፥

- አለርጂስትስ (የአለርጂ እና የአስም ሐኪሞች)
- ዴርማቶሎጂስት (የቆዳ ሐኪሞች)
- ካርዲዮሎጂስት (የልብ ሐኪሞች)
- ኢንዶክሪኖሎጂስት (የስኳር በሽታ እና የታይሮይድ ሐኪሞች)
- ፖዲያትሪስቶች (የእግር ሐኪሞች)
- ኦንኮሎጂስት
- ኦብስቴትሪክስ/ጋይናኮሎጂ (የጽንስና የማህፀን ሕክምና) (OB/Gyn)

ስፔሺያሊስት ማየት ከፈለጉ፣ ነገር ግን Amerigroup DC ለጉብኝቱ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- በ Amerigroup DC መረብ ውስጥ ያለ ሌላ ሐኪም ጋር ቀጠሮ በማስያዝ ሁለተኛ አስተያየት ማግኘት
- በውሳኔያችን ይግባኝ ያቅርቡ (ይመልከቱ35በይግባኝ ላይ)
- ፍትሃዊ ችሎት ይጠይቁ (ይመልከቱ ገጽ35ስለ ፍትሃዊ ችሎቶች)

## የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች

የተወሰኑ አገልግሎቶችን ያለቅድመ ፈቃድ ከእርስዎ PCP ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች ተብለው ይጠራሉ እና ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

### ለሚከተሉት ሪፈራል አያስፈልግዎትም፥

- የእርስዎን PCP ለማየት
- ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥምዎ ሕክምና ለማግኘት
- ለመደበኛ ወይም የመከላከል አገልግሎቶች በመረብዎ ውስጥ ያሉ የእርስዎ የአዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም አገልግሎቶች ለማግኘት (ለሴቶች ብቻ)
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለማግኘት
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች (STIs) አገልግሎቶች ለማግኘት
- ክትባቶች (መርፌዎች) ለማግኘት
- በመረብ ውስጥ የሚገኝ የዓይን ሕክምና አቅራቢ ጋር ለመሄድ

## የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች

የወሊድ መቆጣጠሪያ ወይም ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልግዎትም። ሁሉም የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሚስጥራዊ ናቸው።

የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶችን በAmerigroup DC አቅራቢ መረብ ውስጥ ከሚገኝ ሐኪም ማግኘት ይችላሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልግዎትም። ከእርስዎ PCP ውጪ ሌላ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሐኪም ከመረጡ፣ ለእርስዎ PCP ይንገሯቸው። የእርስዎ PCP ለእርስዎ የተሻለ እንክብካቤ እንዲሰጡ ያግዛቸዋል። ከእርስዎ PCP ጋር ይነጋገሩ ወይም ወደ Amerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ፣ ለወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ።

### የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታል፥

- የእርግዝና ምርመራ
- ለሴቶች እና ለጥንዶቹ የምክር አገልግሎት

- መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ
- የምክር አገልግሎት እና ክትባቶች
- በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ምርመራ
- በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ሕክምና
- የማምከን ሕክምና (21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን ያስፈልጋል እና ከሕክምናው30ቀናት በፊት ቅጹን መፈረም ይጠይቃል)
- የኤችአይቪ/ኤድስ (HIV/AIDS) ምርመራ እና የምክር አገልግሎት

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን አያካትቱም፥**

- መደበኛ የመሃንነት ምርመራዎች ወይም ሕክምናዎች
- ለማምከን ማህጸንን ማውጣት
- በፈቃደኝነት የተከናወነ መሃንነትን ለመለወጥ
- HIV/AIDS ሕክምና
- ጽንስ ማስወረድ

**HIV/AIDS ምርመራ፣ የምክር አገልግሎት፣ እና ሕክምና**

HIV/AIDS ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፥

- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሲኖሮት
- ከራስዎ PCP
- HIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማዕከል

HIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎት የት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)። የኤችአይቪ ሕክምና ካስፈለጎት፣ የእርስዎ PCP ሕክምና እንዲያገኙ ያግዝዎታል። ወይም ለ800-600-4441 (TTY 711) መደወል ይችላሉ። በተጨማሪ ሐኪምዎ ለኤችአይቪ/ኤድስ ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳሎት ካመኑ የቅድመ መጋለጥ ፕሮፊላክሲስ (PrEP) ማግኘት ይችላሉ።

**የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች እና የሐኪም ማዘዣ ያላቸው መድሃኒቶች**

መድሃኒት ቤቶች(ፋርማሲዎች) መድሃኒትዎን የሚያገኙበት ቦታ ነው። ሐኪምዎ የመድሃኒት ማዘዣ ከሰጦት፣ Amerigroup DC መረብ ውስጥ ያለን መድሃኒት ቤት መሄድ መጎብኘት አለብዎ።

በAmerigroup DC መረብ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የመድሃኒት ቤቶች ዝርዝር በAmerigroup የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአቅራቢ ማውጫዎ ወይም ኦንላይን በ provider.amerigroup.com/dc-provider ማግኘት ይችላሉ።

ከከተማ ውጪ ከሆኑ፣ ድንገተኛ ሕክምና፣ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ካስፈለጎት፣

- እየተጓዙ ከሆነ እና መድሃኒትዎን አስቀድመው መሙላት ከፈለጉ፣ የእረፍት ጊዜ አቅርቦት ለመጠየቅ የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች ጋር በ833-214-3604ይደውሉ።
- ለድንገተኛ አገልግሎት፣ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ይሂዱ ወይም ወደ911ይደውሉ።
- ለአስቸኳይ ሕክምና፥
    - የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ። የእርስዎ የPCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ሊገኙ የሚችሉበትን የስልክ ቁጥር ይተዉ። የእርስዎ PCP ወይም ተተኪው ባለሞያ መልሰው ይደውልልዎታል።
    - የእርስዎን PCP ምክር ያክብሩ። ሕክምናውን በምን ያህል ፍጥነት ማግኘት እንዳለብዎ እና ሕክምናውን የት እንደሚያገኙ ሊነገርዎ ይችላሉ።
    - እርዳታ ከፈለጉ የነርስ የእርዳታ መስመር ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## የሐኪም ማዘዣዎ እንዲሞላ፥

- የAmerigroup DC መረብ አካል የሆነ እና ለሥራዎ ወይም ለቤትዎ ቅርብ የሆነ መድሃኒት ቤት ይምረጡ።
- የሐኪም ማዘዣ ካሎት፣ ወደ መድሃኒት ቤቱ ይሂዱ እና ለፋርማሲስቱ የሐኪም ማዘዣዎን እና የእርስዎን የAmerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይስጧቸው።
- እርዳታ ካስፈለጎት፣ እባክዎ ወደ የመድሃኒት ቤት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ833-214-3604 ይደውሉ።

## ማስታወስ የሚያስፈልጉ ነገሮች፥

- ለመድሃኒቶችዎ እንዲከፍሉ መጠየቅ የለብዎትም። መድሃኒት ቤቱ ወይም የመድሃኒት መደብሩ እንዲከፍሉ ከጠየቅዎ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ ሐኪምዎ ለመድሃኒት ከAmerigroup DC የቀደመ ፈቃድ (PA) ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ሐኪምዎ የቀደመ ፈቃዱን ለማግኘት በሚጠባበቁበት ጊዜ፣ እርስዎ መድሃኒቱን የማግኘት መብት አሎት፥
    - እስከ72ሰዓታት ወይም
    - ወይም የመድሃኒቱን አንድ የተሟላ ዙር፣ በቀን ከአንድ ጊዜ ያነሰ የሚወስዱት ከሆነ

## የበሽታ መቆጣጠር

እርስዎ ከባድ በሽታ ካለብዎ ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአእምሮ በሽታ ለመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና ካስፈለጎት፣ የኛ የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም ውስጥ ልናስገባዎ እንችላለን። ይህ ማለት የበሽታ ተቆጣጣሪ ይኖርዎታል ማለት ነው። የበሽታ ተቆጣጣሪ የሚሰራው ለAmerigroup DC ነው እና በሽታዎን ለመቆጣጠር እና ጤናማ ለመሆን የሚያስፈልግዎትን አገልግሎቶች እና መረጃ እንዲያገኙ ያግዝዎታል።

## የህክምና ቅንጅት እና የጉዳይ ፍሰት ፕሮግራሞች

እርስዎ ከባድ በሽታ ካለባችሁ ወይም ለስኳር በሽታ፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የአእምሮ ጤና፣ ወይም አስም ለመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና ካስፈለጎት፥ Amerigroup DC የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን የሚያግዙ ልዩ አገልግሎቶችን እና ፕሮግራሞችን ሊያቀርብልዎ ይችል ይሆናል። እርስዎ በሽታችዎን ለመቆጣጠር እና ጤናዎን ለማሻሻል የሚያስፈልግዎትን አገልግሎቶችን እና መረጃ እንዲያገኙ ለማስቻል የጤና ሕክምና አስተዳዳሪ ይኖርዎታል።

የAmerigroup DC የጉዳይ አስተዳዳሪ በሚከተሉት ሊረዳዎ ይችላል፥

- ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶች ማግኘት፤
- የሕክምና ቀጠሮዎች እና ምርመራዎችን ማዘጋጀት፤
- ትራንስፖርት ማዘጋጀት፤
- ትክክለኛውን አገልግሎት ማግኘትዎን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዘዴዎችን መፈለግ፤
- ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችን ለመርዳት ግብዓቶችን መፈለግ እና ተንከባካቢዎችዎ የዕለት ተዕለት ጭንቀቶችን እንዲቋቋሙ መርዳት፤ እና
- የማህበረሰብ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት።

የኛ ሰራተኞች ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላሉ። እነሱ በተጨማሪ በአሁን ወቅት ለየትኞቹ ፕሮግራሞች እርስዎ እንደተመዘገቡ ሊያሳውቅዎ ይችላሉ። በተጨማሪ ሪፈራል ወይም ከአንድ ፕሮግራም ለመውጣት መጠየቅ ይችላሉ ለበለጠ መረጃ፣ የAmerigroup DC የጉዳይ አስተዳደር ፕሮግራምን በ833-346-1663ያግኙ።

## <u>ከመታመም የሚከላከልልዎ አገልግሎቶች</u>

Amerigroup DC ጤናዎን እንዲጠብቁ ይፈልጋል። እኛ በተጨማሪ የኛ የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች ጋር እንዲመዘገቡ እንፈልጋለን። የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች የማጣሪያ ምርመራዎችን፣ የምክር አገልግሎት እና ክትባቶችን ያካትታሉ።

## የምርመራዎች (“ማጣሪያዎች”) ምክረሀሳቦች

እባክዎ ቀጠሮ ይያዙ እና ለክትትል ምርመራ በየአመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ የእርስዎ PCP ጋር ይሂዱ። በክትትል ምርመራዎ ወቅት ከእርስዎ PCP ጋር ሊያወሯቸው ስለሚችሉ ነገሮች በ "የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች" ክፍል ላይ “የአዋቂ የደህንነት አገልግሎቶች” ዝርዝርን ይመልከቱ።

## እንዴት ጤናማ ሆኖ መቆየት እንደሚቻል

የመከላከል የምክር አገልግሎት ለእርስዎ የሚቀርበው እርስዎ ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ ለማስቻል ነው። በሚከተሉት ነገሮች ላይ የመከላከል የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፥

- ምግብ እና የአካል እንቅስቃሴ
- የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀም
- ሲጋራ ማጨስ ማቆም
- HIV/AIDS መከላከል
- የእርግዝና መከላከያ ሕክምና

## ክትባቶች ወይም "መርፌዎች"

አዋቂ ከሆኑ የተወሰነ ክትባቶች (መርፌዎች) ሊያስፈልግዎ ይችላል። የትኞቹ እንደሚያስፈልግዎ ለማወቅ እባክዎ የእርስዎ PCP ጋር ያውሩ።

## <u>እርግዝና - መውለድ</u>

እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ካሰቡ፣ የአዋላጅ ሐኪምዎ/የማህጸን ሐኪምዎ ጋር ወዲያውኑ መሄድ አስፈላጊ ነው። ይህን ቀጠሮ ከመያዝዎ በፊት የእርስዎን PCP ማየት አያስፈልግዎትም።

## እርጉዝ ከሆኑ፣ እባክዎ ይደውሉ፥

- የኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) በ(202) 727-5355 እርግዝናዎን ሪፖርት ለማድረግ
- የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711)
- የእርስዎ PCP

እርጉዝ ከሆኑ ሊመረመሯቸው የሚገቡ የተወሰኑ ነገሮች አሉ። ይህ ጤናማ እርግዝና፣ ወሊድ፣ እና ህጻን እንዲኖርዎ ለማረጋገጥ ያግዛሉ። ይህ ቅድመ ወሊድ ሕክምና ተብሎ ይታወቃል። ህጻን ልጅዎ ከመወለዱ በፊት የቅድመ ወሊድ ሕክምና ያገኛሉ።

**ያስታውሱ፣ እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከጠረጠሩ፥**
**አልኮል አይጠጡ፣ አደንዛዥ ዕፅ አይጠቀሙ ወይም አያጨሱ።**

## ከወሊድ በፊት እና በኋላ

### ለነፍሰ ጡር ተመዝጋቢዎች ልዩ እንክብካቤ

Taking Care of Baby and Me® ለሁሉም ነፍሰ ጡር ተመዝጋቢዎች የAmerigroup DC ፕሮግራም ነው። ነፍሰ ጡር በሚሆኑበት ጊዜ የእርስዎን ዋና የእንክብካቤ አቅራቢዎን (PCP) ወይም የጽንስ እና የማህፀን ሐኪም (OB/GYN) ማየት በጣም አስፈላጊ ነው። አስቀድመው ልጅ የወለዱ ቢሆንም እንኳን የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው። በፕሮግራማችን፣ ተመዝጋቢዎች የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ እንክብካቤ ለማግኘት መረጃ እና ሽልማቶችን ያገኛሉ።

በተጨማሪ የኛ ፕሮግራም የተወሳሰበ የሕክምና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ነፍሰጡር ተመዝጋቢዎችንም ያግዛል። የነርስ የጉዳይ አስተዳዳሪዎች የሚከተሉትን ለማቅረብ ከእነዚህ ተመዝጋቢዎች ጋር በቅርበት ይሰራሉ፡-

- ትምህርት
- ስሜታዊ ድጋፍ
- የሐኪሞቻቸውን የእንክብካቤ እቅድ እንዲተገብሩ ማገዝ
- እንደ ማዳዳዣ፣ ሴቶች፣ ሕፃናት እና ሕፃናት (WIC)፣ የቤት ውስጥ የጉብኝት ፕሮግራሞች፣ የጡት ማጥባት ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት የመሳሰሉ በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች እና ግብአቶች መረጃ

በተጨማሪ ነርሶች ከሐኪሞች ጋር ይሰራሉ እና ተመዝጋቢዎች ሊፈልጓቸው በሚችሉ ሌሎች አገልግሎቶች ላይ እገዛ ያደርጋሉ። ግቡ ለተመዝጋቢዎች የተሻለ ጤናን እና ጤናማ ሕፃናትን እንዲወለዱ ማድረግ ነው።

**ልጅዎን ከወለዱ በኋላ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) እና ESA ጋር በ(202) 727-5355 ይደውሉ።**

ከወለዱ በኋላ ለድህረ ወሊድ ምርመራ የእርስዎ PCP ወይም OB/GYN ጋር የጉብኝት ቀጠሮ መያዝ አስፈላጊ ነው። ጥሩ ስሜት ሊሰማዎ እና እንደዳኑ ሊያስቡ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከወሊድ በኋላ ሰውነት ለመጠገን ቢያንስ ስድስት ሳምንታት ይወስዳል።

- ጉብኝቱ ከወለዱ በኋላ ከ7እስከ84ቀናት ውስጥ መደረግ አለበት።
- በሲሴክሽን (ኦፕራስዮን) ከወለዱ ወይም ከእርግዝናዎ ወይም ከወሊድ ጋር የተያያዙ ችግሮች ካጋጠምዎት፣ የእርስዎ PCP ወይም OB/GYN የአንድ ወይም የሁለት ሳምንት ምርመራ ለማድረግ እንዲመለሱ ሊጠይቅዎ ይችላል። ይህ የድህረ ወሊድ ምርመራ ተደርጎ አይቆጠርም። ከወለዱ በኋላ ከ7 እስከ84ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ለድህረ ወሊድ ምርመራ ወደ አቅራቢዎ ተመልሰው መሄድ እና መታየት ያስፈልግዎታል።

## <u>የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች</u>

### በAmerigroup DC የሚሸፈኑ አገልግሎቶች

ከዚህ በታች ያለው ዝርዝር የሁሉንም የAmerigroup DC ተመዝጋቢዎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እና ጥቅማጥቅሞችን ያሳያል። ለአንዳንድ ጥቅማጥቅሞች፣ የተወሰነ የእድሜ ገደብ ላይ መሆን ወይም ለአገልግሎቱ ልዩ ፍላጎት ሊኖርዎ ይገባል። Amerigroup DC በመረብ ውስጥ ወዳለ አቅራቢ ወይም ሆስፒታል ከሄዱ፣ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ላሉ ማንኛውም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ አያስከፍልዎትም።

እርስዎ Amerigroup DC የተወሰነ የጤና እንክብካቤን የሚሸፍን መሆን አለመሆኑ ላይ ጥያቄ ካሉት፣ ወደ Amergropu DC የምዝገባ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

| ጥቅማጥቅም | እርስዎ የሚያገኙት |
|---|---|
| **የአዋቂ የደህንነት ምርመራ አገልግሎቶች** | • ክትባቶች<br>• በግብረስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች መደበኛ የማጣሪያ ምርመራ<br>• HIV/AIDS ማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና ምክር<br>• የጡት ካንሰር ምርመራ<br>• የማህጸን ካንሰር ምርመራ (ለሴቶች ብቻ)<br>• የኦስቲዮፖሮሲስ (አጥንት መሳሳት) ምርመራ (ለድህረ ማረጥ ለሴቶች)<br>• የ HPV ምርመራ<br>• የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ (ለወንዶች ብቻ)<br>• የአብዶሚናል አኦርቲክ አኑሪዝም ምርመራ<br>• ከመጠን ያለፈ ውፍረት ምርመራ<br>• የስኳር በሽታ ምርመራ<br>• የከፍተኛ የደም ግፊት እና ኮሌስትሮል (የሊፒድ በሽታ) ምርመራ<br>• የድብርት ምርመራ<br>• የኮሎሬክታል ካንሰር ምርመራ (እድሜያቸው50እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች)<br>• ሲጋራ የማጨስ የምክር አገልግሎት<br>• የምግብ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የምክር አገልግሎት<br>• የአእምሮ ጤና የምክር አገልግሎት<br>• የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ ምርመራ |
| **የጥርስ ሕክምና ጥቅማጥቅሞች** | • አጠቃላይ የጥርስ ህክምና (መደበኛ እና ድንገተኛ ህክምናን ጨምሮ)<br>  ○ በየ6 ወሩ የሚደረግ አጠቃላይ የጥርስ ምርመራን ጨምሮ የጥርስ እና የድድ እንክብካቤ እና ህክምና<br>  ○ ቀላል እና ውስብስብ የቀዶ ጥገና አገልግሎቶች እና መንቀል<br>  ○ ድንገተኛ የጥርስ ሕክምና<br>  ○ መሞላት<br>  ○ በየ6ወሩ ማጽዳት እና የፍሎራይድ ህክምናዎች<br>  ○ ለህክምና አስፈላጊ በሚሆንበት ከፊል ሰው ሰራሽ ጥርስ<br>  ○ ኤክስሬይ (በየ3ዓመት ጊዜ ውስጥ ለ1ጊዜ የተሟሉ ተከታታይ) |

| | |
|---|---|
| | ○ ሰው ሰራሽ ጥርሶች (በየ5ዓመቱ አንድ አዲስ ጥንድ) እና የሰው ሰራሽ ጥርስ ጥገና<br>○ የአፍ ውስጥ ቀዶ ጥገና<br>○ $1000 ገደብ በአንድ የካላንደር ዘመን ለሚሰጡ አገልግሎቶች<br>○ ሆስፖፒታል ውስጥ ተኝቶ መታከምን የሚጠይቅ ማንኛውም የጥርስ ሕክምና አገልግሎት የቀደመ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል<br>○ በምርጫ የሚደረግ የቀዶ ጥገና ሕክምና አጠቃላይ ማደንዘዥን የሚጠይቅ<br>*መደበኛ የኦርቶዶንቲክ ሕክምናን አያካትትም |
| **የዳይለሲስ (የኩላሊት እጥበት) አገልግሎቶች** | • በሳምንት እስከ3ጊዜያት ሕክምና (በቀን አንድ ጊዜ ብቻ) |
| **ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME) እና አላቂ የሕክምና አቅርቦቶች (DMS)** | • ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME)<br>• አላቂ የሕክምና አቅርቦቶች (DMS) |
| **የቤተሰብ ምጣኔ** | • የእርግዝና ምርመራ፤ ለሴቷ የምክር አገልግሎት<br>• መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ<br>• በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ማምከን (ከቀዶ ጥገናው30ቀናት በፊት የተመዝጋቢው ፊርማ ያለው የጸደቀ የማምከን ቅጽ ያስፈልጋል)<br>• ምርመራ፣ ምክር እና ክትባቶች (የ HPV ን ጨምሮ)<br>• በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ምርመራ እና የመከላከል ሕክምና<br>• ነርስ አዋላጅ ሐኪም እና የዳውላ አገልግሎቶች |
| **የመስማት ጥቅማጥቅሞች** | • ከመስማት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ የመስሚያ መሳሪያዎች እና የመስሚያ መሳሪያ ባትሪዎች |
| **የቤት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች** | • የቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፥<br>○ የነርሲንግ እና የቤት ውስጥ የጤና እርዳታ እንክብካቤ<br>○ በቤት ጤና ኤጀንሲ የሚሰጥ የቤት ውስጥ የጤና እርዳታ አገልግሎቶች<br>○ የአካል ህክምና፣ኦኩፔሽናል ቴራፒ፣የንግግር ፓቶሎጂ እና የኦዲዮሎጂ አገልግሎቶች |
| **የሆስፒታል አገልግሎቶች** | • የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች (የመከላከል፣የመመርመሪያ፣የሕክምና፣ የማገገሚያ ወይም የማስታገሻ አገልግሎቶች)<br>• የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች (የሆስፒታል ቆይታ) |
| **ላቦራቶሪ እና የኤክስሬይ አገልግሎቶች** | • የላብራቶሪ ምርመራዎች እና ኤክስሬዮች |
| **የነርሲንግ ሆም እንክብካቤ** | • በነርሲንግ ሆም ውስጥ በሰለጠኑ ነርስ የሙሉ ጊዜ እንክብካቤ ለተከታታይ30ቀናት ድረስ ያክል |

| | |
|---|---|
| **የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች (የሃኪም ማዘዣ ያላቸው መድሃኒቶች)** | • በAmerigroup DC የመድሃኒት ቅጽ ላይ ያሉ በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች። የመድሃኒት ቅጹን በ myamerigroup.com/DC ወይም የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በመደወል ማግኘት ይችላሉ |
| **የእግር በሽታ ሐኪም** | • ለእግር ችግሮች ልዩ ሕክምና<br>• በሕክምና አስፈላጊ ሲሆን መደበኛ የእግር ሕክምና |
| **ዋና የእንክብካቤ አገልግሎቶች** | • የመከላከል፣ ቀላል፣ እና ከባድ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በአጠቃላይ በእርስዎ PCP የሚሰጥ |
| **የማገገሚያ አገልግሎቶች** | • ከባድ ጉዳት ወይም ሌሎች የሕክምና ክስተቶችን ተከትሎ አሰራርን ለማሻሻል ለመርዳት በሕክምና አስፈላጊ መሆኑን አስቀድሞ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን። ይህ የአካል፣ የንግግር፣ እና ኦኩፔሽናል ቴራፒን ያካትታል። |
| **የስፔሺያሊስት አገልግሎቶች** | • ልዩ ስልጠና በወሰዱ ሐኪሞች ወይም የላቀ ልምድ ባላቸው ነርሶች የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>• አብዛኛውን ጊዜ ሪፈራል ያስፈልጋል |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | • ወደ ሐኪም ቀጠሮዎች እና ከዚያ መልስ የትራንስፖርት አገልግሎት በ DHCF የሚሸፈኑ አገልግሎቶችን ጨምሮ |

**በAmerigroup DC የማይሸፈኑ አገልግሎቶች**

- ከስሜቲክ የቀዶ ጥገና
- የሙከራ ወይም የምርመራ አገልግሎቶች፣ የቀዶ ጥገናዎች፣ ሕክምናዎች፣ እና መድሃኒቶች
- የክሊኒካል ሙከራ ፕሮቶኮል አካል የሆኑ አገልግሎቶች
- ጽንስ ማስወረድ፣ ወይም በፈቃደኝነት ጽንስን ማቋረጥ፣ በፌደራል ህጉ መሰረት የሚቻል አይደለም
- የመሃንነት ሕክምና
- በሕክምና አስፈላጊ ያልሆኑ አገልግሎቶች
- ክፍት የልብ ቀዶ ጥገና
- የዓይን ሕክምና
- የሰውነት አካል ንቅለተከላ
- የተወሰኑ የምክር ወይም የሪፈራል አገልግሎቶች በሃይማኖታዊ ወይም የሞራል እምነቶች ምክንያት በ Amerigroup DC ሽፋን ላይሰጣቸው ይችላል። ለበለጠ መረጃ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶችን በ800-600-4441 ያግኙ

## የህክምና ሽግግር

Amerigroup DC ለእርስዎ አዲስ ከሆነ፣ ለመጀመሪያ90ቀናት የተያዙትን የሐኪም ቀጠሮዎች እና የመድሃኒት ማዘዣዎችን እንዳሉ መቆየት ይችላሉ። አቅራቢዎ በአሁን ወቅት በ Amerigroup DC መረብ ውስጥ ካልሆኑ፣ በAmerigroup DC የአቅራቢ መረብ ውስጥ ያለ አዲስ አቅራቢ እንዲመርጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ሐኪምዎ የ Amerigroup DCመረብን ከለቀቁ፣ ሌላ አቅራቢ ለመምረጥ ጊዜ እንዲኖርዎ በ15የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን። Amerigroup DC አቅራቢዎን ካቋረጠ፣ የሚያበቃበት ጊዜ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት በ30የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን።

## ሌላ ጠቃሚ መረጃ

### ቦታ ከቀየርኩስ?

- የመገኛ መረጃዎን ወቅታዊ ያድርጉ በመስመር ላይ በwww.districtdirect.dc.gov።
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

### ልጅ ከወለድኩስ?

- የዲሲ የኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል ጋር በ(202) 727-5355 ይደውሉ።
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

### ልጅ በማደጎ ከወሰድኩስ?

- ESA የለውጥ ማዕከል ጋር በ(202) 727-5355 ይደውሉ።

### ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞትስ?

- ESA የለውጥ ማዕከል ጋር በ(202) 727-5355 ይደውሉ።
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

### የኔን MCO እንዴት መቀየር እንደምችል?

- የእርስዎን MCO መቀየር በሚከተለው ሁኔታ መቀየር ይችላሉ፥
  - የመጀመሪያው የምዝገባ ቀንዎን ተከትሎ ባሉት90የካላንደር ቀናት ወይም ከዲስትሪክቱ የምዝገባ ማስታወቂያዎ ከደረሶት ከ90የካላንደር ቀናት በኋላ፣ ኋለኛው የሆነው የትኛውም።
  - በክፍት የምዝገባ ወቅት በዓመት አንድ ጊዜ።
  - ጊዜያዊ የብቃት ማጣት ክፍት የምዝገባ ወቅት እንዲያመልጥዎ ካደረገ።
  - ዲስትሪክቱ MCO ላይ ቅጣት ከጣለ ወይም ምዝገባውን ካገደ።
    - ጥሩ ምክንያት/ሰበብ ካሎት በማንኛውም ጊዜ፣ ለምሳሌ፥ ከአገልግሎት መስጫ ክልል ከወጡ፤
    - Amerigroup DC በሞራል ወይም ሐይማኖታዊ ተቃውሞዎች ምክንያት፣ የሚያስፈልግዎትን አገልግሎት(ቶች) ካልሸፈነ፤
    - እርስዎ ተያያዥ አገልግሎቶችን በተመሳሳይ ጊዜ እንዲከናወን ከፈለጉ፣ እና ሁሉም ተያያዥ አገልግሎቶች ካልተገኙ፣ እና አቅራቢዎ አገልግሎቶቹን ለየብቻ ማግኘት አስጊ ነው ብለው ከወሰኑ።
    - MCO የእርስዎን ዘር፣ ጾታ፣ ብሄር፣ ብሄራዊ ምንጭ፣ ሐይማኖት፣ የአካል ጉድለት፣ እርግዝና፣ እድሜ፣ የጄኔቲክ መረጃ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታዊ መለያ፣ የግል አቀራረብ፣ የቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ የፖለቲካ ዝንባሌ፣ እና የገቢ ምንጭ ወይም የመኖሪያ አድራሻን መሠረት በማድረግ አድልዎ እንደፈጸመብዎ ካመኑ፤ ወይም

- ደካማ ጥራት ያለው ሕክምና ያገኙ ሆኖ ከተሰማዎት፣ ሽፋን ላላቸው አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፣ ወይም የእርስዎ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ላይ ልምድ ያላቸው አቅራቢዎች ተደራሽ እንዳልሆኑ ከተሰማዎ።

- የዲሲ ጤናማ ቤተሰቦች (D.C. Healthy Families) ከክፍት የምዝገባ ወቅት ሁለት ወራት በፊት ደብዳቤ ይልክልዎታል። ደብዳቤው MCOዎችን እንዴት መቀየር እንደሚችሉ ይነግርዎታል።
- የእርስዎን MCO ሲቀይሩ፣ የሚያስፈልግዎን እንክብካቤ ማግኘት እንዲቀጥሉ የእርስዎ የጤና እንክብካቤ መረጃዎ ወደ መረጡት አዲስ MCO ይሸጋገራል።

**ከAmerigroup DC የጤና እንክብካቤ ማግኘት አይፈቀድልዎትም በሚከተሉት ሁኔታዎች፥**

- ለማንኛውም ሌላ የህክምና እርዳታ ፕሮግራም ወይም የጤና መድን ብቁ ከሆኑ።

.

**የD.C.(ዲሲ) መንግስት በሚከተሉት ምክንያቶች እርስዎን ከAmerigroup DC ሊያስወጣዎ ይችላል፥**

- የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ካደረጉ፤
- የጤና ሕክምና ማጭበርበር ከፈጸሙ፤ ወይም
- የተመዝጋቢ ግዴታዎችዎን ካላከበሩ።

**ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ቢደርሰኝስ?**

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ለሆነ ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ከደረሶት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።

**ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ይከፍላሉ?**

- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት ማግኘት እንዳለብዎ ከወሰኑ እና ከAmerigroup DC የጽሁፍ ፈቃድ ከሌሎት፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ መክፈል ይኖርብዎታል።
- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት ለማግኘት ከወሰኑ፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ እንደሚከፍሉ መስማማትዎን የሚገልጽ መግለጫ መፈረም አለብዎ።
- አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ ***በፊት*** የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ማሳየት እና ለሐኪሞችዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ መሆንዎን መንገር ሁሉጊዜ ያስታውሱ።

**የቀደመ መመሪያ**

የቀደመ መመሪያ የሕክምና እንክብካቤዎን አስመልክቶ ስለእርስዎ በመሆን ምርጫዎችን የሚያደርግ ሰው እንዲመርጡ ያስችልዎታል። በተጨማሪ የቀደመ መመሪያ ፍላጎቶችዎን ለሌሎች ለመንገር በማያስችል ሁኔታ በጣም ቢታመሙ ምን ዓይነት የሜዲካል ሕክምና ማግኘት እንደሚፈልጉ ለመናገር ያስችልዎታል።

ስለ ቀደመ መመሪያዎ ከቤተሰብ፣ ከእርስዎ PCP፣ ወይም እርስዎን ከሚያግዙ ሌሎች ሰዎች ጋር ማውራት ጠቃሚ ነው።

የቀደመ መመሪያ መሙላት እና መፈረም ከፈለጉ፣ በቀጣይ ቀጠሮዎ ላይ የእርስዎ PCP እንዲያግዝዎ ይጠይቋቸው፣ ወይም የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)፣ እና እነሱ እርስዎን ያግዛሉ።

## ሐኪሞችዎን እንዴት እንደምንከፍላቸው ልዩ መረጃ

እርስዎ Amerigroup DC ልዩ የፋይናንስ ትብብር ከAmerigroup DC ሐኪሞች ጋር ያላቸው መሆን ወይም አለመሆኑን የማወቅ መብት አሎት።

እባክዎ ለዚህ መረጃ ወደ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## ማጭበርበር ምንድን ነው?

ማጭበርበር ከባድ ጉዳይ ነው። ማጭበርበር ማለት የማይገባዎትን የተወሰነ ጥቅማጥቅምን ወይም ክፍያን ለማግኘት ሀሰተኛ መግለጫዎችን ወይም ፍሬ ነገሮችን መግለጽ ማለት ነው። የአቅራቢዎች የማጭበርበር ምሳሌ፥ ላልተሰጡ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶች የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ። የተመዝጋቢዎች የማጭበርበር ምሳሌ ማለት የColumbia ዲስትሪክት ዙሪያ ውጪ እየኖሩ Columbia ውስጥ እንደሚኖሩ በሐሰት መግለጽ።

የማጭበርበር ድርጊትን ከጠረጠሩ፣ እባክዎ ለኛ ያሳውቁን። እራስዎን መግለጽ ወይም ስምዎን መስጠት አያስፈልግዎትም። ማጭበርበር ምን እንደሆነ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ የAmerigroup DC ድረገጽን በ myamerigroup.com/DC ይጎብኙ። ማጭበርበርን ሪፖርት ለማድረግ፣ ይደውሉ ወደ Amerigroup DC የትግበራ የስልክ መስመር ጋር፣ **877-660-7890** ወይም የዲሲ የጤና እንክብካቤ የፋይናንስ ማጭበርበር ዲፖርትመንት የስልክ መስመር ጋር በ**1 (877) 632-2873** ይደውሉ።

## <u>ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች</u>

Amerigroup DC እና የዲስትሪክቱ መንግስት ሁለቱም እርስዎ ስለሚያገኙት እንክብካቤ፣ ወይም Amerigroup DC ስለሚያቀርብልዎ አገልግሎቶች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ዘዴ አላቸው። ቅሬታዎን ከዚህ በታች እንደተገለፀው ማቅረብ ይችላሉ።

## ቅሬታዎች

- እርስዎ ላይ በተፈጠረ አንድ ነገር ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። የሚከተሉት ቅሬታ ማቅረብ ሊያስፈልግዎ የሚችሉባቸው ምክንያቶችን ምሳሌ ያካትታሉ፥
    - በአክብሮት እንዳልተሰተናገዱ ተሰምትዎታል
    - ባገኙት የጤና ሕክምና እንክብካቤ አልረኩም
    - ቀጠሮ ለማግኘት በጣም ረጅም ጊዜ ወስዷል

- ቅሬታ ለማቅረብ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) መደወል አለብዎ።
- በተጨማሪ ሐኪምዎ ለእርስዎ ቅሬታ ሊያቀርብልዎ ይችላሉ።

ያልተደሰቱበት ነገር ከተፈጠረ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። Amerigroup DC አብዛኛውን ጊዜ በ90ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል ነገር ግን ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜም ሊጠይቁ ይችላሉ (ነገር ግን በአጠቃላይ ከ104 የካላንደር ቀናት ሊበልጥ አይችልም)።

ቅሬታ በጽሁፍ Amerigroup DC ጋር ለማቅረብ፣ በፖስታ ይላኩ ለ Centralized Appeals Processing | Amerigroup District of Columbia, Inc. | P.O. Box 62429 | Virginia Beach, VA 23466-2429።

## ይግባኞች

- ጥቅማጥቅሞችዎ አለአግባብ እንደተከለከሉ፣ እንደተቀነሱ፣ እንደዘገዩ፣ ወይም እንደቆሙ ከተሰማዎ፣ Amerigroup DC ጋር ይግባኝ የማቅረብ መብት አሎት። ደውለው ይግባኝዎን በስልክ ካቀረቡ፣ Amerigroup DC ይግባኝዎን በደብዳቤ አጠቃለው ይጽፉታል እና ለእርስዎ ቅጂውን ይልካሉ። ደብዳቤውን በጥንቃቄ ማንበብዎን ያረጋግጡ።
- ይግባኝዎ በደረሰ በ30የካላንደር ቀናት ውስጥ ይግባኝዎ ላይ በAmerigroup DC ውሳኔ ይሰጣል።
- Amerigroup DC መረጃ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለጋቸው እና ዲስትሪክቱ ይህ ለእርስዎ የሚጠቅም እንደሆነ ከወሰነ፣ ወይም እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ ተጨማሪ ጊዜ ከጠየቃችሁ፣ Amerigroup DC የውሳኔ ጊዜውን በ14የካላንደር ቀናት ሊጨምረው ይችላል። Amerigroup DC ስለ ማራዘሚያው የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል።
- ፖስታው ላይ፣ ስለ ይግባኝዎ የAmerigroup DC የውሳኔ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይደርስዎታል።
- Amerigroup DC በይግባኝዎ ላይ በሰጠው ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ፣ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- Amerigroup DC ጋር ይግባኝ ለማቅረብ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።
- ይግባኝ በጽሁፍ Amerigroup DC ጋር ለማቅረብ፣ በፖስታ ይላኩ ለ Centralized Appeals Processing | Amerigroup District of Columbia, Inc. | P.O. Box 62429 | Virginia Beach, VA 23466-2429።

## ፍትሃዊ ችሎቶች

እርስዎ Amerigroup DC ጋር ባቀረቡት ይግባኝ ውጤት ካልረኩ፣ የዲሲ የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር "ፍትሃዊ ችሎት" መጠየቅ ይችላሉ።

የፍትሃዊ ችሎት ጥያቄ ለማቅረብ፣ የዲስትሪክቱ መንግስት ጋር ይደውሉ ወይም ይጻፉ ወደ፥

District of Columbia Office of Administrative Hearings
Clerk of the Court
441 Fourth St. NW
Room N450
Washington, DC 20001
የስልክ ቁጥር፥ (202) 442-9094

## የመጨረሻ ቀናቶች፥

- ጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ60የካላንደር ቀናት ውስጥ ይግባኝዎን ማቅረብ አለብዎ።
- የAmerigroup DC የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ከ120የካላንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ አለብዎ።
- በፍትሃዊ ችሎትዎ ወይም ይግባኝዎ ወቅት ጥቅማጥቅምዎን ማግኘት መቀጠል ከፈለጉ፣ ፍትሃዊ ችሎቱ ወይም የይግባኝ ችሎቱ ከሚከተለው ጊዜ በኋላ የሚከተሉትን እንዲያደርግልዎ መጠየቅ አለብዎ፥
  - በAmerigroup DC የጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያን በላከበት ፖስታ ላይ ካለው ቀን ወይም የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን በ10 የካላንደር ቀናት ወይም
  - የታቀደው የAmerigroup DC እርምጃ ተፈጻሚነቱ ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ (ወይም፣ በሌላ አባባል፣ ጥቅማጥቅሙ የሚቆምበት ቀን)።

አቅራቢዎ እርስዎን በመወከል ይግባኝ ሊያቀርብልዎ ወይም ፍትሃዊ ችሎት ሊጠይቅልዎ ይችላሉ።

## የተፋጠነ (ድንገተኛ) ቅሬታዎች እና የይግባኞች ሂደት

ይግባኝዎ ድንገተኛ መሆኑ ከተወሰነ፣ Amerigroup DC በ72ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል። አንድ ይግባኝ ድንገተኛ ነው ተብሎ የሚቆጠረው እርስዎ መደበኛውን የይግባኝ ሂደት የጊዜ ማዕቀፍ ቢጠብቁ ለእርስዎ ጎጂ ወይም የሚያሰቃይ ከሆነ ነው።

HIV/AIDS፣ የአእምሮ በሽታ፣ ወይም አፋጣኝ ትኩረት የሚፈልግ ሌላ ሁኔታ ባለባቸው ተመዝጋቢዎች የሚቀርቡ ሁሉም ይግባኞች ይግባኙ በቀረበ በ24ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ አግኝተው ለተመዝጋቢው ይገለጽላቸዋል።

## **በቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ሂደት ውስጥ እርስዎ ያሉት መብቶች**

- እርስዎ ፍትሃዊ ችሎት የማግኘት መብት አሎት። እርስዎ Amerigroup DC ጋር አንድ ደረጃ ያለው የይግባኝ ሂደት ካቀረቡ በኋላ፣ ከአስተዳደር ችሎት ቢሮ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን አንስቶ ከ120የካላንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ አለብዎ።
- Amerigroup DC ይግባኝዎን የሚመለከት ማስታወቂያ ካልሰጡት ወይም በጊዜ ማስታወቂያ ካልሰጡት፣ ከዚያ በኋላ የይግባኝ ሂደቱ የተሟላ እንደሆነ ይቆጠራል፣ እና መቀጠል እና ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ይግባኝዎ ወይም ፍትሃዊ ችሎቱ በሚታይበት ጊዜ የከለከልንዎትን ጥቅማጥቅም እያገኙ የመቆየት መብት አሎት። በፍትሃዊ ችሎት ወቅት ጥቅማጥቅምዎን ይዞ ለመቆየት፣ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ፍትሃዊ ችሎቱን መጠየቅ አለብዎ - ይህ ጊዜ ከ10የካላንደር ቀናት ያጠረ ሊሆን ይችላል።
- እርስዎ በቅሬታ እና የይግባኝ ሂደት ወቅት ከAmerigroup DC አንድ ሰው እርዳታ የማግኘት መብት አሎት።
- እራስዎን የመወከል ወይም በቤተሰብ ተንከባካቢ፣ ጠበቃ፣ ወይም ሌላ ወኪል የመወከል መብት አሎት።
- ለማንኛውም ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች መቆያ እንዲመቻችልዎ የመጠየቅ መብት አሎት።
- እርስዎ በቂ የ TTY/TTD ችሎታዎች እና ማየት ለተሳናቸው አገልግሎቶች የማግኘት መብት አሎት።
- እርስዎ በቂ የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች የማግኘት መብት አሎት።
- እርስዎ ከቅሬታዎ፣ ይግባኝዎ፣ ወይም ፍትሃዊ ችሎቱ ጋር የተያያዙ ሁሉንም ሰነዶች የማየት መብት አሎት።

ስለ ቅሬታዎቹ እና ይግባኞቹ/ፍትሃዊ ችሎት ሂደት ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።

## **<u>የግላዊነት ልምድ ማስታወቂያ</u>**

ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የሚመለከት የሕክምና መረጃ አገልግሎት ላይ እንዴት ሊውል እንደሚችል እና ይፋ እንደሚሆን እና ይህን መረጃ እርስዎ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት።

ስለ ጤናዎ እና ስለ ገንዘብዎ ያለው መረጃ ሚስጥራዊ ነው። ሕጉ PHI በመባል የሚጠራውን ይህን ዓይነት መረጃን፣ ለአባሎቻችን ደህነነቱን በጠበቀ መልኩ እንድንጠብቅ ያስገድደናል። ያ ማለት እርስዎ አሁን አባል ከሆኑ ወይም ቀደሞ አባል ከነበሩ፣ የመረጃዎ ደህንነት የተጠበቀ ነው ማለት ነው።

ለጤና እቅዳችን ብቁ ሆነው ከተመዘገቡ በኋላ ስለእርስዎ ከMedicaid የስቴት ኤጀንሲዎች እና የህጻናት የጤና መድን ፕሮግራም መረጃ እናገኛለን። በተጨማሪም ለጤና እንክብካቤዎ እንድንፈቅድ እና ክፍያ እንድንፈጽም፣ ከእርስዎ ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች እና ሆስፒታሎች መረጃ እናገኛለን።

የፌደራል ህግ በጽሁፍ የተነገረንን፣ ወይም በኮምፒዩተር የተቀመጠን PHI ለመጠበቅ ማድረግ ስለሚገባን ነገሮች ለእርስዎ መንገር እንዳለብን ያስገድደናል። በተጨማሪ እኛ ደህንነቱን እንዴት እንደምንጠብቅ ልንነግርዎ ይገባል። PHIን ለመጠበቅ፦-

- በወረቀት ላይ (ቁሳዊ ተብሎ የሚጠራ)፣ እኛ፦-
  - ቢሮዎቻችንን እና ፋይሎቻችንን እንቆልፋለን
  - ሌሎች እንዳያገኙት የጤና መረጃ የያዙ መረጃዎችን እናስወግዳለን
- በኮምፒውተር ላይ የተቀመጠ (ቴክኒካል ተብሎ የሚጠራው)፣ እኛ፦-
  - ትክክለኛዎቹ ሰዎች ብቻ እንዲገቡ የይለፍ ቃሎችን እንጠቀማለን
  - ሲስተሞቻችንን ለመከታተል ልዩ ፕሮግራሞችን እንጠቀማለን
- ለእኛ፣ ለሐኪሞች ወይም ለስቴት የሚሰሩ ሰዎች የሚጠቀሙት ወይም የሚያጋሩት፣ እኛ፥
  - የመረጃ ደህንነትን ለመጠበቅ መመሪያዎችን እናወጣለን (ፖሊሲዎች እና ሥነ ሥርዓቶች ተብለው ይጠራሉ)
  - ለእኛ የሚሰሩ ሰዎች መመሪያዎቹንን እንዲከተሉ እናስተምራቸዋለን

## እኛ የእርስዎን PHI መጠቀም እና ማጋራት የምንችለው መቼ ነው?

የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን የእርስዎን PHI ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎ ወይም ለሚከፍልልዎ እርስዎ ለመረጡት ሰው ልናጋራ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ፣ **ያለእርስዎ** ይሁንታ ልንጠቀምበት እና ልናጋራው እንችላለን፦-

- **ለህክምና እንክብካቤዎ (ህክምና)**
  - ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች እርስዎ የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ እንዲሰጡ ለመርዳት
- **ለክፍያ ምክንያቶች**
  - ለእርስዎ እንክብካቤ ክፍያ ከሚጠይቁን ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጋር መረጃ ለመጋራት
  - የጤና እንክብካቤ ወይም አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት እንደምንከፍልልዎ ከተናገርን
  - እርስዎን ለመደገፍ እና ያሉትን ጥቅማጥቅሞች እንዲያገኙ ለማገዝ
- **ለጤና አጠባበቅ ጉዳይ ምክንያቶች (ሥራዎች)**
  - የኦዲት፣ ማጭበርበር እና አላግባብ መጠቀምን የመከላከል ፕሮግራሞችን፣ እቅድ ማውጣትን እና የዕለት ተዕለት ሥራን ለመርዳት
  - ፕሮግራሞቻችንን የተሻሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችን ለማግኘት

  የእርስዎን PHI ለጤና መረጃ ልውውጦች ለክፍያ፣ ለጤና እንክብካቤ ስራዎች እና ለህክምና ልንሰጥ እንችላለን። ይህንን የማይፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን ለበለጠ መረጃ myamerigroup.com/DC ይጎብኙ

- **ለሕዝብ ጤና ምክንያቶች**
  - የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ሰዎችን ከመታመም ወይም ከመጎዳት እንዲጠብቁ ለመርዳት
- **ለእንክብካቤዎ እገዛ ለሚያደርጉ ወይም ለሚከፍሉ ሌሎች ሰዎች ጋር**
  - የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎ ወይም ለሚከፍልልዎ እርስዎ ለመረጡት ሰው
  - ስለራስዎ መናገር የማይችሉ ከሆነ እና ለእርስዎ የተሻለ ከሆነ፣ ለጤና እንክብካቤዎ እገዛ ከሚያደርግልዎ ወይም ከሚከፍልልዎ ሰው ጋር

ለሕክምናዎ፣ ክፍያ፣ የእለት ተለት ሥራ፣ የምርምር ጥናት ወይም ከታች ለተዘረዘሩት ሌሎች ነገሮች ውጪ የእርስዎን PHI ከመጠቀማችን ወይም ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ይሁንታ በጽሁፍ ማግኘት አለብን። ስለ እርስዎ ከሐኪምዎ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎችን ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን የጽሁፍ ይሁንታ ማግኘት አለብን። በተጨማሪ የእርስዎን PHI እኛ የምንሸጥ ከሆነ ወይም ለገበያ የምንጠቀምበት ወይም የምናጋራው ከሆነ የእርስዎ የጽሁፍ ይሁንታ ያስፈልገናል።

በጽሁፍ የሰጡትን ይሁንታን መተው እንደሚፈልጉ በጽሁፍ ሊነግሩን ይችላሉ። እኛ መመለስ አንችልም የእርስዎ ይሁንታ ባለበት ወቅት የተጠቀምነውን ወይም ያጋራነውን። ነገር ግን ወደፊት የእርስዎን PHI መጠቀም ወይም ማጋራት እናቆማለን።

## ሌሎች መንገዶች - ወይም ህጉ የሚፈቅድልን - የእርስዎን PHI እንድንጠቀም፥

- ፖሊስን እና ሌሎች ህግ የሚያስከብሩ ሰዎችን ለመርዳት። ለምሳሌ፣ አላግባብ መጠቀምን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ PHI ን ልንጠቀም እንችላለን።
- ስንጠየቅ ፍርድ ቤቱን ለመርዳት። ለምሳሌ፣ በፍርድ ቤት የሚያያዙ እንደ አቤቱታ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ የመሳሰሉ ህጋዊ ሰነዶች ላይ ምላሽ ለመስጠት PHI ልንጠቀም እንችላለን።
- ለጤና ቁጥጥር ኤጀንሲዎች ወይም ለሌሎች ለመንግስት አንዳንድ ስራዎችን ለሚሰሩ መረጃ ለመስጠት። ለምሳሌ፣ ለኦዲት ወይም ለፈተና መረጃ እንሰጣለን።
- የእርስዎን ስም እና የሞት መንስኤ ለማወቅ እንዲረዳቸው ለሬሳ ምርመራ ሐኪሞች፣ የህክምና መርማሪዎች ወይም የቀብር አስፈጻሚዎች።
- የሰውነት ክፍሎችዎን ለሳይንስ ወይም ለጥናት ምርምር ለመስጠት ሲጠይቁ ለመርዳት። ለምሳሌ፣ ሲሞቱ የሰውነት ክፍልዎን ለመለገስ ከተስማሙ መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን።
- እርስዎን ወይም ሌሎች ከመታመም ወይም ክፉኛ ከመጎዳት ለመጠበቅ። ለምሳሌ፣ እርስዎ ወይም ሌሎች በአስቸኳይ ሁኔታ ውስጥ ጉዳት እንዳይደርስባችሁ ለመከላከል የእርስዎን PHI ልናጋራ እንችላለን።
- ለሠራተኞች ካሳ መረጃ ለመስጠት። ለምሳሌ፣ በስራ ላይ ሆነው ከታመሙ ወይም ከተጎዱ የእርስዎን መረጃ ልናጋራ እንችላለን።

## መብቶችዎ ምንድን ናቸው?

- የእርስዎን PHI ለማየት እና ቅጂውን ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። ነገር ግን ሙሉ የሕክምና መረጃዎ የለንም። ሙሉ የህክምና መረጃዎን ቅጂ ከፈለጉ፣ ሐኪምዎን ወይም የጤና ክሊኒክዎን ይጠይቁ።
- የሆነ ችግር እንዳለ ወይም የጎደለ ነገር አለ ብለው ካሰቡ ያለንን የእርስዎን የሕክምና መረጃ እንድንቀይረው እኛን መጠየቅ ይችላሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ የእርስዎን PHI እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ። ነገር ግን በጥያቄዎ መስማማት የለብንም ። ለምሳሌ፣ PHI የክሊኒካል ማስታወሻዎች አካል ከሆነ እና በህግ ሊለቀቅ የማይችል ከሆነ ጥያቄዎ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።
- ካለን የእርስዎ አድራሻ ውጪ ወዳለ አድራሻ ወይም በተወሰነ ሌላ መንገድ PHI እንድንልክልዎ እኛን መጠየቅ ይችላሉ። ባለን የእርስዎ አድራሻ መላክ እርስዎን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ይህን ማድረግ እንችላለን።
- ባለፉት ስድስት ዓመታት የእርስዎን PHI ለሌላ ሰው ያጋራንበትን ሁሉንም መረጃ እንድንነግርዎ ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህ ለጤና እንክብካቤ፣ ለክፍያ፣ ለዕለትተዕለት የጤና እንክብካቤ ሥራ ወይም እዚህ ባልዘረዘርናቸው ሌሎች ምክንያቶች ያጋራንበትን ጊዜ አይዘረዝርም።
- የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በኢሜይል እንዲላክልዎ የጠየቁ ቢሆንም እንኳን የወረቀት ቅጂ እንዲላክልዎ በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ።
- ለአንድ አገልግሎት ሙሉዉን ክፍያ ከከፈሉ፣ ስለዚያ አገልግሎት መረጃውን ለእኛ እንዳያጋሩ ሐኪምዎን መጠየቅ ይችላሉ።

## እኛ ምን ማድረግ አለብን?

- ህጉ በዚህ ማስታወቂያ ከገለጽነው ውጪ የእርስዎን PHI ሚስጥራዊ ማድረግ እንዳለብን ያስገድዳል።
- ህጉ ስለ ሚስጥራዊነት እንድናደርግ የሚያስገድደን ምን እንደሆነ ለእርስዎ መንገር አለብን።
- በዚህ ማስታወቂያ እናደርጋለን ብለን የገለጽናቸውን ነገሮች ማድረግ አለብን።
- እርስዎ ከጠየቁ እና አደጋ ላይ ከሆኑ፣ የእርስዎን PHI ወደ ሌላ አድራሻ ወይም መደበኛ ከሆነው ፖስታ ውጪ በሌላ መንገድ መላክ አለብን።
- እንዳናጋራው ከነገሩን በኋላ የእርስዎን PHI ማጋራት ካለብን ለእርስዎ መንገር አለብን።
- እኛ እዚህ እናደርጋቸዋለን ብለን ከገለጽናቸው በላይ የስቴት ህጎች ማድረግ እንዳለብን የሚያስገድዱ ከሆነ፣ እነዚህን ህጎች እንከተላለን።
- የእርስዎ PHI እንደተጣሰ ካሰብን እኛ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።

### እኛ ልናገኝዎ እንችላለን

እኛ፣ ተባባሪዎቻችን እና/ወይም አቅራቢዎቻችንን ጨምሮ፣ አውቶማቲክ የስልክ መደወያ ስርዓት እና/ወይም ቀድሞ የተቀዳ መልእክትን በመጠቀም፣ ገመድ አልባ የስልክ ቁጥርን ጨምሮ ወደሚሰጡን ማንኛውም የስልክ ቁጥሮች ላይ እንድንደውል ወይም የጽሁፍ መልእክት እንድንልክ ተስማምተዋል። እነዚህ የስልክ ጥሪዎች ወይም የጽሁፍ መልእክቶች ስለህክምና አማራጮች፣ ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞች እና አገልግሎቶች፣ ምዝገባ፣ ክፍያ፣ ወይም የክፍያ መጠየቂያ ሊሆኑ የሚችሉ ስሊሆን ነገር ግን በዚህ የተገደቡ አይደሉም።

### ጥያቄዎች ካሉትስ?

ስለ የኛ የሚስጥራዊነት መመሪያችን ጥያቄዎች ካሉት ወይም መብቶችዎን መጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 ይደውሉ። መስማት የተሳነዎ ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎ ፣ ይደውሉ TTY 711።

### አቤቱታ ካሉትስ?

እኛ እዚህ ያለነው ለማገዝ ነው። የእርስዎ PHI ደህንነቱ እንዳልተጠበቀ ከተሰማዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ወይም የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንትን ማግኘት ይችላሉ።

### ለጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቾች መምሪያ ይጻፉ ወይም ይደውሉ፦

Office for Civil Rights
U.S. Department of Health and Human Services
200 Independence Ave. SW
Washington, DC 20201
ስልክ፥ 1-800-368-1019
TDD: 1-800-537-7697

ይህን የጤና መድን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ (HIPAA) ማስታወቂያ እና የእርስዎን PHI ደህንነት የምንጠብቅባቸውን መንገዶች የመቀየር መብታችን የተጠበቀ ነው። እንዲያ ከሆነ፣ እኛ ስለለውጦቹ በመጽሄቶች እንነግርዎታለን። በተጨማሪም በድረገጽ በ myamerigroup.com/pages/privacy.aspx ላይ እንለጥፋቸዋለን።

### ዘር፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ እና የፆታ ማንነት

ስለ እርስዎ ዘር፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ እና የፆታ ማንነት መረጃ ልንቀበል እንችላለን። ይህን መረጃ በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተገለጸው እንጠብቀዋለን።

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት እንጠቀማለን፥

- የሚያስፈልግዎትን መረጃ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ
- የጤና ውጤቶችን የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞችን ለመፍጠር
- የጤና ትምህርት መረጃ ለማዘጋጀት እና ለመላክ
- ስለ ቋንቋ ፍላጎቶችዎ ለሐኪሞች ለማሳወቅ
- የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ለመስጠት

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት **አንጠቀምበትም** ፡-

- የጤና መድን ለመስጠት
- ለአገልግሎቶች ምን ያክል ለማስከፈል ለመወሰን
- ጥቅማጥቅሞችን ለመወሰን
- ላልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ለመግለጽ

## የግል መረጃዎ

የስቴት ህጎች የHIPAA የሚስጥራዊነት መመሪያ ላይ ካለው በላይ ግዴታ የሚጥሉብን ከሆነ ያንን እናከብራለን። በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተናገርነው የግል መረጃን (PI) ልንጠይቅ፣ ልንጠቀም እና ልናጋራ እንችላለን። የእርስዎ PI ለህዝብ ይፋ አይደለም እና እርስዎ ማን እንደሆኑ ይነግረናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚወሰደው ለመድን ዓላማ ነው።

- የእርስዎን PI ስለእርስዎ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ለመወሰን ልንጠቀም እንችላለን፡-
  - ጤና
  - ልማዶች
  - የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎች
- ስለ እርስዎ PI ከሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ልናገኝ እንችላለን ለምሳሌ፡-
  - ሐኪሞች
  - ሆስፒታሎች
  - ሌሎች የመድን ኩባንያዎች
- በአንዳንድ ሁኔታዎች የእርስዎን ይሁንታ ሳናገኝ ከኩባንያችን ውጪ ላሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች PI ልናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ስራችንን ለማስኬድ እንዲረዱን ከምንቀጥራቸው የይገባኛል ጥያቄዎች እና የሂሳብ አከፋፈል አቅራቢዎች ጋር PI ልናጋራ እንችላለን።
- ማንኛውንም ነገር ከማድረጋችን በፊት የመከልከል እድል ለእርስዎ ለመስጠት እናሳውቅዎታለን።
- የእርስዎን PI እንድንጠቀም ወይም እንድናጋራ ካልፈለጉ ለኛ እንዴት እንደሚያሳውቁን እንነግርዎታለን።
- የእርስዎን PI የማየት እና የመቀየር መብት አሎት።
- የእርስዎ PI ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እናረጋግጣለን።

## የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ

የጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ፕሮግራም ከእርስዎ MCO የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ እርስዎን የሚያግዝ የColumbia ዲስትሪክት መንግስት ፕሮግራም ነው። የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፥

- ማግኘት የሚገባዎን የጤና እንክብካቤ መብት ማብራራት፤
- የጤና እንክብካቤዎን የሚመለከቱ ጥያቄዎችዎን እና ስጋቶችዎ ላይ ምላሽ መስጠት፤
- የ MCO ተመዝጋቢ በመሆንዎ ያሎትን መብቶች እና ግዴታዎችን እንዲረዱ ማገዝ።
- የሚያስፈልግዎትን አስፈላጊ የሕክምና አገልግሎቶች እንዲያገኙ መርዳት።
- የጤና እንክብካቤዎ ጥራትን በሚመለከት ሊኖርዎ የሚችሉ ጥያቄዎችን እና ስጋቶችን መመለስ።
- ከሐኪምዎ ጋር ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ያለብዎትን ችግሮች እንዲፈቱ ማገዝ።
- ከ MCO ጋር ያሉ አቤቱታዎችን እና ችግሮችን ለመፍታት እርስዎን መረዳት።
- የይግባኝ ሂደቶች ላይ ማገዝ፤ እና
- የፍትሃዊ ችሎት ጥያቄ ለማቅረብ እርስዎን መርዳት

የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂን ለማግኘት፣ እባክዎ ይደውሉ (202) 724-7491 ወይም 1 (877) 685-6391 ከክፍያ ነጻ። የጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ ወይም ፍትሃዊ ችሎቶች ላይ ውሳኔ አይሰጥም።

የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ የሚገኘው በ፥

One Judiciary Square
441 Fourth St. NW
Suite 250 North
Washington, DC 20001
ስልክ፥ (202) 724-7491
ፋክስ፥ (202) 442-6724
ከክፍያ ነጻ ቁጥር፥ 1(877) 685-6391
ኢሜይል፥ healthcareombudsman@dc.gov

## ትርጉሞች

| | |
|---|---|
| **የቀደመ መመሪያ** | እርስዎ ከታመሙ ወይም ከተጎዱ እና ስለራስዎ መናገር ባይችሉ ሌሎች ስለሚፈልጉት እና የማይፈልጉት የጤና እንክብካቤ እንዲያዉቁ የሚያደርግ፣ በጽሁፍ የሆነ፣ እርስዎ የፈረሙት ህጋዊ ወረቀት ነው። |
| **ጠበቃ** | እርስዎ የሚፈልጉትን የጤና እንክብካቤ እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያግዝዎ ሰው። |
| **ይግባኝ** | ይግባኝ ማለት Amerigroup DC የጤና ሕክምና አገልግሎቶችን ወይም ላገኟቸው አገልግሎቶች ክፍያ በመከልከል በሚሰጠው አንድ ውሳኔ ሳይስማሙ ሲቀር የሚያቀርቡት ልዩ አቤቱታ ነው። በተጨማሪ በውሳኔው ካልተስማሙ እያገኙ ያሉትን አገልግሎቶች ለማስቀም ይህን ዓይነት ልዩ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። |
| **ቀጠሮ** | የእርስዎን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ለማሟላት እርስዎ እና ሐኪምዎ ጊዜ እና ቀን መድቡ። |
| **የሕክምና አስተዳዳሪ** | የሚያስፈልግዎትን ሕክምና፣ ድጋፍ፣ እና ጤናማ ሆነው ለመቆየት የሚያስፈልግዎትን መረጃ እንዲያገኙ እርስዎን ለመርዳት ከAmerigroup DC ጋር የሚሰራ ሰው ነው። |
| **ምርመራ** | *የማጣሪያ ምርመራን ይመልከቱ* |
| **የወሊድ መቆጣጠሪያ** | የወሊድ መቆጣጠሪያ ጋር የተያያዙ አቅርቦቶች። |
| **ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ለሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በAmerigroup DC ክፍያ የሚከፈልባቸው። |
| **መርዛማ ነገር ከሰውነት ውስጥ ማስወጣት** | እንደ አደንዛዥ እጽ እና የአልኮል መጠጥ የመሳሰሉ ጎጂ ነገሮችን ከሰውነት ማስወገድ። |
| **የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም** | ከባድ በሽታ ያለባቸው ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአእምሮ በሽታ የመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና የሚፈልጉ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና አገልግሎቶች እንዲያገኙ የሚረዳ ፕሮግራም። |
| **ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME)** | ቤትዎ ውስጥ እንዲጠቀሙት ሐኪምዎ የሚጠይቅዎ ወይም የሚያዝዎ ልዩ የሕክምና መሳሪያ። |
| **ድንገተኛ ሕክምና** | ለከባድ፣ ድንገተኛ፣ አንዳንድ ጊዜ ለህይወት አስጊ ለሆነ ሁኔታ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎ ሕክምና። |
| **ተመዝጋቢ** | በAmerigroup D የአቅራቢ መረብ አማካኝነት የጤና እንክብካቤ የሚያገኝ ሰው። |

| | |
|---|---|
| **የተመዝጋቢ መታወቂያ (ID) ካርድ** | እርስዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ መሆንዎን ሐኪሞችዎ፣ ሆስፒታሎች፣ መድሃኒት ቤቶች፣ እና ሌሎች እንዲያውቁት የሚያደርግ ካርድ። |
| **ፍትሃዊ ችሎት** | ይግባኝዎ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ የዲሲ የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። |
| **የቤተሰብ ምጣኔ** | አገልግሎቶቹ የእርግዝና ምርመራዎች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ እና የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎትን ያካትታል። |
| **የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሕክምና ሐኪም** | መላውን ቤተሰብ ሊያክም የሚችል ሐኪም። |
| **ቅሬታ** | በሚያገኙት ሕክምና፣ ወይም Amerigroup DC በሚሰጠው የጤና ሕክምና አገልግሎቶች ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ለማቅረብ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ። |
| **የመምሪያ መጽሃፍ** | ይህ መጽሀፍ ስለ Amerigroup DC እና ስለኛ አገልግሎቶች መረጃ ይሰጥዎታል። |
| **መስማት የተሳነው** | በሚገባ መስማት የማይችሉ ከሆነ ወይም መስማት የተሳኖት ከሆኑ። |
| **ክትባት** | መርፌ ወይም ክትባት። |
| **የውስጥ ደዌ ሕክምና ሐኪም** | የአዋቂዎች እና እድሜያቸው ከ14ዓመት በላይ የሆኑ ልጆች ሐኪም። |
| **የአስተርጓሚ/የትርጉም አገልግሎቶች** | የራስዎን ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር ለማውራት ወይም ከሐኪምዎ ጋር ወይም ከሆስፒታሉ ጋር ለማውራት ከAmerigroup DC የሚያገኙት እርዳታ። |
| **የተቀናጀ የእንክብካቤ እቅድ (MCP)** | እርስዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና ሕክምና እና የጤና አገልግሎቶች እንዲያገኙ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚከፍለው ኩባንያ። |
| **የወሊድ ጊዜ** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና የምትቆይበት እና ከወሊድ በኋላ ያለው አጭር ጊዜ። |
| **የአእምሮ ጤና** | አንድ ሰው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚያስበው፣ የሚሰማው፣ እና የሚያደርገው ድርጊት። |
| **የመረብ አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ እና የAmerigroup DC አካል የሆኑ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ለተሰጠ የጤና ሕክምና Amerigroup DC ክፍያ የማይፈጽምበት። |
| **አዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም (OB/GYN)** | አዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም፤ እርግዝናን ጨምሮ፣ የሴት ጤናን ለማከም የሰለጠነ ሐኪም። |

| | |
|---|---|
| **ከመረብ ውጭ አቅራቢዎች** | ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ጤናዎን የሚንከባከቡ ሰዎች የAmerigroup DC አካል አይደሉም። |
| **መድሃኒት ቤት** | መድሃኒትዎን የሚያገኙበት ቦታ። |
| **የሐኪም የጥቅማጥቅም እቅድ** | ሐኪምዎ ከAmerigroup DC ጋር ማንኛውም ልዩ ትብብር ካላቸው ይነግርዎታል። |
| **የድህረ ወሊድ ሕክምና** | ልጅዎን ከወለደች በኋላ አንዲት ሴት የምታገኘው የጤና ሕክምና ነው። |
| **የቅድመ ወሊድ ሕክምና** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና በምትቆይበት ጊዜ ሁሉ የሚሰጥ የሕክምና እንክብካቤ ነው። |
| **የመድሃኒት ማዘዣ** | ሐኪምዎ ለእርስዎ የሚያዙት መድሃኒት፤ የመድሃኒት ማዘዣውን ለማምጣት ወደ መድሃኒት ቤት መውሰድ አለብዎ። |
| **የመከላከል የምክር አገልግሎት** | ጤናማ ሆነው ለመቆየት ወይም ከመታመም ወይም ከመጎዳት እራስዎን ለመከላከል ስለሚያስችሉ ዘዴዎች ከአንድ ሰው ጋር ማውራት ሲፈልጉ። |
| **ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)** | አብዛኛውን ጊዜ ለእርስዎ ሕክምና የሚሰጡት ሐኪም። |
| **የቀደመ ፈቃድ** | የጤና እንክብካቤ ወይም ሕክምና ለማግኘት ከAmerigroup DC የሚያገኙት የጽሁፍ ፈቃድ። |
| **የአቅራቢ ማውጫ** | የAmerigroup DC መረብ አካል የሆኑ የሁሉም አቅራቢዎች ዝርዝር። |
| **አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሪፈራል** | በሌላ ሐኪም እንዲታዩ እርስዎን ለመላክ ዋና ሐኪምዎ የሚሰጠው የጽሁፍ ማስታወሻ። |
| **መደበኛ ህክምና** | ከዋና የሕክምና አቅራቢዎ ወይም ዋና የሕክምና አቅራቢዎ ከላክዎ ሐኪም የሚያገኙት መደበኛ ሕክምና። መደበኛ የሕክምና ምርመራ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ማጣሪያ ምርመራ፣ እና እንደ የስኳር በሽታ፣ አስም፣ እና የደም ግፊት የመሳሰሉ የጤና ችግሮችን በተመለከተ የሚያገኙት መደበኛ ሕክምናን ያካትታል። |
| **የማጣሪያ ምርመራ** | እርስዎ ጤናማ መሆንዎን ለማወቅ ሐኪምዎ ወይም ሌላ የጤና ሕክምና አቅራቢ ሊያከናውኑት የሚችሉ ምርመራ። |
| **የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች** | ከዋና ሐኪምዎ የጽሁፍ ማስታወሻ ወይም ሪፈራል ሳያስፈልግዎ ሊያገኟቸው የሚችሉ የተወሰኑ አገልግሎቶች። |
| **አገልግሎቶች** | ከሐኪምዎ ወይም ከሌላ የጤና ሕክምና አቅራቢ የሚያገኙት ሕክምና። |

| | |
|---|---|
| **ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች** | ሌሎች አዋቂዎች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ወይም የተለየ የጤና ሕክምና እና ሌሎች ልዩ አገልግሎቶች የሚፈልጉ አዋቂዎች። |
| **ስፔሺያሊስት** | ልዩ ሕክምና ለመስጠት የሰለጠነ ሐኪም፥ እንደ የጆሮ፣ የአፍንጫ፣ የጉሮሮ፣ ወይም የእግር ሐኪም። |
| **የስፔሺያሊቲ ሕክምና** | የጤና ሕክምናው የሚሰጠው ልዩ ዓይነት የጤና ሕክምና ለመስጠት በሰለጠኑ ሐኪሞች ወይም ነርሶች ነው። |
| **የማምከን ሕክምናዎች** | ልጅ መውለድ ወደፊት ሳይፈልጉ ሲቀር ሊያደርጉት የሚችሉት የቀዶ ጥገና። |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | ወደ ቀጠሮ ቦታዎ ለመሄድ ከAmerigroup እርዳታ። የሚያገኙት የትራንስፖርት ዓይነት የሚወሰነው በሚያስፈልግዎ የሕክምና ዓይነት ነው። |
| **ሕክምና** | ከሐኪምዎ የሚያገኙት ሕክምና። |
| **አስቸኳይ ህክምና** | ወዲያውኑ ሳይሆን፣ በ24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ ሕክምና። |
| **ማየት የተሳነው** | በሚገባ ማየት የማይችሉ ከሆነ ወይም ማየት የተሳኖት ከሆነ። |

Amerigroup

District of Columbia


Amerigroup District of Columbia, Inc.

የተመዝጋቢ አገልግሎቶች፦

609 H St. NE, Ste. 200

Washington, DC 20002

800-600-4441 (TTY 711) (ከክፍያ ነፃ)

myamerigroup.com/dc


DHCF

Department of Health Care Finance

WE ARE WASHINGTON DC

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

MURIEL BOWSER, MAYOR


This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.